ምስለ-ቅር ወልዱ።
ወላዲቱ፡ አምላክ

ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ናት ፤
ይህችስ ሰዓት ምን ያህል የምታስጨንቅ ናት ፤
መንፈስ ቅዱስ ከሰማየ ሰማያት የሚወርድባት፤

How awesome is this day and how marvelous this hour wherein the Holy Spirit will descend from heaven

ይህን መሥዋዕቱን የሚሰውርባትና
የሚያከብርባት። በጽሞናና በመፍራት ቁሙ ፤
የእግዚአብሔር ሰላም ከእኔና ከእናንተ ጋራ ይሆን
ዘንድ ጸልዩ ።

and overshadow and hallow this sacrifice. In quietness and in fear, arise and pray that the peace of God be with me and with all of you.

ሕዝብ - አሜን Amen

ሕዝብ

ኩሉ ዘገብራ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ ኢይበል ፈላሲ ዘገብአ ኀበ እግዚአብሔር ይፈልጠኒኑ እምሕዝቡ ኩሉ ዘገብራ ለጽድቅ፤ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ

በጎን የሚያደርግ ሰንበትንም የሚያከብር ሁሉ ጻድቅ ነው። ወደ እግዚአብሔር አምልኮ የገባ መጻተኛ ከሕዝቡ ሁሉ ይለየኝ ይሆን? አይበል በጎ ያደረገ ሰንበትንም የሚያከብር ጻድቅ ነው።

Blessed is he who does blessed deeds and honors the Sabbath. Let him not question whether he will be outcast from the multitudes if he was to enter into the worship of God. Blessed is he who does blessed deeds and honors the Sabbath.

ሃሌ ሉያ! እመቦ ብእሲ እምእመናን ዘቦአ ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ወኢሰምአ መጻሕፍተ ቅዱሳተ ወኢተዐገሰ እስከ ይፈጽሙ ጸሎተ ቅዳሴ....

ሃሌ ሉያ በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገስ ከቁርባን ባይቀበል ከቤተ ክርስቲያን ይውጣ

Halleluia! If there be anyone of the faithful that hath entered the church at the time of mass and hath not heard the holy Scriptures, and hath not waited until they finish the prayer of the Mass, and hath not received the holy communion, let him be driven out of the church:

ወኢተመጠወ እምቍርባን ይሰደድ እምቤተ ክርስተያን እሰመ አማሰነ ሕገ እግዚአብሔር ወአስተሐቀረ ቁመተ ቅድመ ንጉሥ ሰማያዊ ንጉሠ ሥጋ ወመንፈስ ከመዝ መሐሩነ ሐዋርያት በአብጥሊሶሙ።

የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና የነፍስና የሥጋ ንጉስ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ በክርስቶስ ፊት መቆምን አቃሏልና ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዲህ ሲሉ አስተማሩን

for he hath violated the law of God and disdained to stand before the heavenly King, the King of Body and Spirit. This the Apostles have taught us in their canons.

ሕዝብ

አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ እንተ ውስቴታ መና ኅቡእ ኅብስት ዘወረደ እምሰማያት ወሃቤ ሕይወት ለኩሉ ዓለም

ንጹሕ የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ፤ በውስጧ የተሰወረ መና የነበረባት፤ ከሰማያት የወረደ ኅብስት ለዓለም ሁሉ ድኅነት የሚሰጥ

Thou art the pot of pure gold wherein is hidden the manna, the bread which came down from heaven giving life unto all the world.

ካህን

ንጹሕ ወጣዕም ወበረከት ለእለ ይሰትዩ

እምደምከ ክቡር አላትዬን በአማን አሜን።

በእውነት ሰው የሆንህ አምላክ ሆይ ንጹሕ ጣዕም በረከትም ከክቡር ደምህ ለሚጠጡ ይሁን፤ አሜን

Purity, sweetness and blessing be to them who honestly drink of Thy precious blood. Amen.

ካህን

ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ
ኩሉ ዓለም አምላክነ - አሜን።

ዓለሙን ሁሉ የያዘ እግዚአብሔር
አብ ቡሩክ ነው - አሜን።

Blessed be the Lord, almighty Father, our God – Amen.

ካህን

ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ
ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ - አሜን።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ወልድ ዋሕድም ቡሩክ ነው-
አሜን።

And blessed be the only Son, our Lord and Saviour Jesus Christ - Amen.

ካህን

ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጸራቅሊጦስ

መጽንዒ ወመንጽሔ ኩልነ - አሜን።

ሁላችንን የሚያነጻ ፣ የሚያጸና መንፈስ

ቅዱስም ቡሩክ ነው - አሜን።

And blessed be the Holy Spirit, the Paraclete, the comforter and cleanser of us all - Amen.

ካህን - ስብሐት ወክብር ይደሉ ለሥሉስ ቅዱስ አብ
ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዕሩይ ኩሎ ጊዜ
ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ልዩ ሦስት ለሚሆኑ ሁልጊዜም ለተካከሉ ለአብ
ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ይገባል
ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Glory and honour are due to the holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit, always coequal, both now and ever and unto the ages of ages. Amen

ካህን

ጸልዩ አበውየ ወአኀውየ ላዕሌየ ወላዕለ ዝንቱ መሥዋዕት።

አባቶቼና ወንድሞቼ በእኔ ላይ መሥዋዕቱም ላይ ጸልዩ።

My fathers and my brothers, pray for me and for this sacrifice.

ንፍቅ ካህን - እግዚአብሔር ይስማዕከ ኵሎ ዘሰአልከ ወይትወከፍ መሥዋዕተከ ወቍርባንከ ከመ መሥዋዕተ መለከጼዴቅ ወአሮን ወዘካርያስ ካህናተ ቤተ ክርስቲያኑ ለበኵር።

እግዚአብሔር የለመንከውን ሁሉ ይስማህ። የቤተ ክርስቲያኑ ካህናቱ የሚሆኑ የመልከ ጼዴቅንና የአሮንን የዘካርያስንም መሥዋዕት እንደ ተቀበለ መሥዋዕትህን ቍርባንህንም ይቀበልልህ። ሁሉም አቡነ ዘበሰማያት ይበሉ።

May God hear you in all that you have asked and accept your sacrifice and offering like the sacrifice of Melchisedec and Aaron and Zacharias, the priests of the church of the firstborn. Our Father ……

ካህን

ተዘከረኒ አ አቡየ ቀሲስ በጸሎትከ ቅድስት።

አባቴ ሆይ ክብርት በምትሆን በጸሎትህ አስበኝኞ

Remember me, my father priest,

in your holy prayers.

ካህን

እግዚአብሔር ይዕቀባ ለክህነትከ ወይትወከፍ መሥዋዕተከ ወቍርባንከ በብሩህ ገጽ። ሥመር እግዚኦ ከመ ታድኅንኒ።

እግዚአብሔር ክህነትህን ይጠብቃት፤ መሥዋዕትህንና ቍርባንህንም በብሩህ ገጽ ይቀበልልህ ፤ አቤቱ እኔን ታድነኝ ዘንድ ማዳንን ውደድ።

The Lord keep your priesthood and accept your sacrifice and offering with a gracious countenance. Be pleased, Lord, to save me.

ካህን

አሐዱ አብ ቅዱስ
አሐዱ ወልድ ቅዱስ
አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።

አንዱ አብ ቅዱስ ነው፤
አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው፤
አንዱ መንፈስ ቅዱስም ቅዱስ ነው።

One is the Holy Father, one is the Holy Son, one is the Holy Spirit.

ሕዝብ

በአማን አብ ቅዱስ በአማን ወልድ ቅዱስ
በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።

አብ በእውነት ቅዱስ ነው፤ ወልድ
እውነት ቅዱስ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ
በእውነት ቅዱስ ነው።

Truly the Father is holy, truly the Son is holy, truly the Holy Spirit is holy.

ካህን

ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ኩልክሙ አሕዛብ
ምእመናን ሁላችሁም እግዚአብሔርን አመስግኑት

Praise the Lord, all ye nations.

ሕዝብ

ወይሴብሕዎ ኩሎሙ ሕዝብ
ሕዝብም ሁሉ ያመሰግኑታል

And praise Him, all ye people.

ካህን

እስመ ጸንዐት ምሕረቱ ላዕሌነ

ምሕረቱ በእኛ ላይ ጸንታለችና

For His merciful kindness is great toward us.

ሕዝብ

ጽድቁሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም

የእግዚአብሔርስ ቸርነቱ ለዘለዓለሙ ይኖራል።

And the Truth of the Lord endured forever.

ካህን (ካህኑን በመከተል ሕዝቡ ይህንን ይድገሙ)

ስብሐት ለአብ ፤ ወወልድ ፤ ወመንፈስ ቅዱስ

ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል

Glory be to the Father and to the Son and to the Holy Spirit

ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን
ሃሌ ሉያ።

ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን
ሃሌ ሉያ።

Both now and ever and world without end. Amen.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለን

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ጸሎተ አኩቴት ዘቅዱስ ባስልዮስ

የቅዱስ ባስልዮስ የምስጋና ጸሎት

The "Prayer of Thanksgiving" of St. Basil.

ነአኩቶ ለገባሬ ሠናያት ላዕሌነ እግዚአብሔር መሐሪ አቡሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ለእኛ በጎ ነገርን ያደረገ ይቅር ባይ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ይቅር ባይ የጌታችን የአምላካችንና

We give thanks unto the doer of good things unto us, the merciful God, the Father of our Lord and our God and our Savior Jesus Christ: for He hath covered

እስመ ሰወረነ ወረድኦነ ዐቀበነ ወአቅረበነ ወተወክፈነ ኀቤሁ። ወተማኅፀነነ። ወአጽንዐነ። ወአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት።

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሰውሮናልና ረድቶናልና ጠብቆ አቅርቦናልና ወደ እርሱም ተቀብሎናልና አጽንቶ ጠብቆናልና እስከዚች ሰዓት አድርሶናልና።

us and succored us, He hath kept us and brought us nigh and received us unto Himself, and undertaken our defense, and strengthened us, and brought us unto this hour.

ንስኣሎ እንከ ከመ ይዕቀበን በዛቲ ዕለት ቅድስት ኩሎ መዋዕለ ሕይወትነ ወበኩሉ ሰላም አኃዜ ኩሉ እግዚአብሔር አምላክነ።

አሁንም ክብርት በምትሆን በዚች ዕለት በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በፍጹም ሰላም ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር ይጠብቀን ዘንድ እንለምነው።

Let us therefore pray unto Him that the Almighty Lord our God keep us in this holy day and all the days of our life in all peace.

ዲያቆን/Deacon

ጸልዩ

Pray ye.

ካህን

ሁሉን የያዝህ ጌታችን እግዚአብሔር የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በሥራው ሁሉ ላይ ስለ ሥራው ሁሉ በሥራውም ሁሉ ውስጥ እናመሰግንሃለን ስውረኸናልና ረድተኸናልና ጠብቀኸናልና ወዳንተ አቅርበህ ጠብቀኸናልና አጽንተህ ጠብቀኸናልና እስከዚችም ሰዓት አድርሰኸናልና።

Master, Lord God Almighty, the Father of our Lord and our God and our Savior Jesus Christ, we render Thee thanks upon everything, for everything and in everything, for Thou hast covered us and succored us, hast kept us and brought us nigh, and received us unto Thyself, and undertaken our defense, and strengthened us and brought us unto this hour

ዲያቆን

ሳሉ ወአስተብቍዑ ከመ ይምሐረነ እግዚአብሔር ወይሣሃል ላዕሌነ

እግዚአብሔር ይምረን ዘንድ በእኛም ላይ ይቅር ይል ዘንድ እሹ ለምኑ።

Entreat ye and beseech that the Lord have pity upon us and be merciful to us

ወይትወከፍ ጸሎተ ወስእለተ እምነ ቅዱሳኒሁ በእንቲኣነ
በዘይሤኒ ኩሎ ጊዜ ይረስየነ ድልዋነ ከመንንሣእ
እምኡታፌ ምሥጢር ቡሩክ ወይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

ስለኛ ከቅዱሳን ጸሎትን ልመናንም ይቀበል
ዘንድ፤ ሁልጊዜ ማረ ነገር ቡሩክ ከሚሆን ምሥጢር
አንድነት እንድንቀበል የበቃን ያደርገን ዘንድ።

receive our prayer and supplication from His saints on our behalf, according to what is expedient at all times, so that He may make us ready to partake of the communion of the blessed sacra-ment and forgive us our sins.

ሕዝብ

ኪርየላይሶን

Kyrie eleison.

ካህን

ስለዚህ እንለምንሃለን ከቸርነትህም እንሻለን ሰውን የምትወድ ሆይ! ክብርት የምትሆን ይህችን እለት እን ድንፈጽም ስጠን ፤ የሕይወታችንን ዘመን ሁሉ በፍጹም ሰላም አንተን ከመፍራት ጋራ

For this cause we pray and entreat of Thy goodness, O lover of man, grant us to complete this holy day and all the days of our life in all peace along with Thy fear.

ቅንዓትን ሁሉ መከራውንም ሁሉ የሰይጣን
ንም ሥራ ሁሉ የክፎች ሰዎችንም ምክር
የጠላትንም መነሣት የተሰወረውንና
የተገለጸውን።

All envy, all trial, all the working of Satan, the counsel of evil, and all the uprisings of adversaries, secret and open.

አቤቱ ከእኔ አርቅ። ከሕዝብህም ሁሉ ያንተ ከሚሆን ከዚህም ቅዱስ ቦታ በጎውን ነገር ሁሉ ያማረውንና የሚሻለውን እዘዝልን፤ እባቡን ጊንጡንም የጠላትንም ኃይል ሁሉ እንረግጥ ዘንድ ሥልጣንን የሰጠኸን አንተ ነህና። ወደ መከራ አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ።

remove far from me, and from all Thy people, and from this Thy holy place All good things, that are expedient and excellent, com-mand Thou for us, for Thou art He Who has given us power to tread upon serpents and scorpions and upon all the power of the enemy.

አንድ ልጅህ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ም ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ፍቅር ብሎ ባደረገው ቸርነትና ይቅርታ። በርሱ ያለ ምስጋና ክብር ጽን ዕ ከእርሱ ጋር ላንተ ይገባል፤ ካንተ ጋራ ትክክል ማኅየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅድስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Lead us lest we wander into temptation, but deliver us and rescue us from all evil in the grace and loving kindness, shown by the love -towards mankind of Thine only-begotten Son, our Lord, God, and Saviour Jesus Christ, through Whom to Thee with Him and with the Holy Spirit, the life-giver, Who is coequal with Thee are due glory, honour, and dominion, both now and ever, and unto ages of ages. Amen.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሢ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለን

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ካህን (የሐዋርያት የመባ ጸሎት)

ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን። ከሁሉ በላይ በምትሆን በከበረች በአንዲት ቤተ ክርስቲያን መባ ስለሚያገቡ መሥዋዕቱን ቀደምያቱን

"The prayer of Oblation" of the Apostles.

And again let us beseech the Almighty Lord, the Father of the Lord our Savior Jesus Christ, on behalf of those who bring an oblation within the one holy universal church, a sacrifice, first-fruits, tithes, a thank offering,

ካሥር አንዱን የመታሰቢያ ምስጋና ብዙውንና ጥቂቱን የተሰወረውንና የተገለጸውን ይሰጡ ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብሎ መንግሥተ ሰማያትን ይሰጥ ዘንድ ለሁሉ በረከትን የሚያድልበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን አምላካችን እግዚአብሔር።

a memorial, whether much or little, in secret or openly, and of those who wish to give and have not wherewith to give, that He accept their ready mind, that He vouchsafe to them the heavenly kingdom; power over all works of blessing belongs to the Lord our God.

ንፍቅ ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ እለ ያበውኡ መባኦ

መባ ስለሚያገቡ ሰዎች ጸልዩ

Pray for them who bring an oblation.

ሕዝብ

ተወከፍ መባኦሙ ለኣኃው ወተወከፍ መባኦን ለኣኃት ለነኒ ተወከፍ መባኦነ ወቍርባነነ

የወንድሞችን መባ ተቀበል የእኅቶቻንም መባ ተቀበል፤ የእኛንም መባችንንና ቍርባናችንን ተቀበል።

Accept the oblation of our brethren, accept the oblation of our sisters, and ours also accept, our oblation and our offering.

ካህን

ሁሉን የምትገዛ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ! አን ለምንሃለን እንማልድሃለንም ከሁሉ በላይ በምትሆን ባን ዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መባ ስለሚያገቡ ሰዎች መሥዋዕቱን መጀመሪያውን ካሥር አንዱን የመታሰቢያ ምስጋናን ብዙውንና ጥቂቱን የተሰወረውንና የተገለጸውን ይሰጡም ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት

Lord our God who art Almighty, we pray Thee and beseech Thee for them that bring an oblation within the one holy universal church, a sacrifice, first-fruits, tithes, a thank offering, a memorial, whether much or little, in secret or openly, and for those who wish to give

ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብለህ ለሁሉም
የበረከትን ዋጋን ስጥ ፤ አድል ፈንታ ትሆን ዘንድ።
በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል ፤
ከርሱ ጋር ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም
ለዘላለሙ ፤ አሜን።

and have not where with to give. Thy acceptance of their ready mind grant Thou unto every one: let the recompense of blessing be a portion to all of them: through Thy only begotten Son, through whom to Thee with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሢ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለን

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ካህን - የጎብስት ጸሎት

Priest:- ("The prayer of Oblation.")

መምህሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ከቀዳማዊ አብ ጋራ አንድ የምትሆን ፣ ንጹሕ የሚሆን የአብ ቃል ፣ የማሕየዊ መንፈስ ቅዱስም ቃል ፣

O my Master, Jesus Christ, co-eternal pure Word of the Father, and Word of the Holy Spirit, the life giver, Thou art the bread of life

ከሰማያት የወረድህ የሕይወት ኅብስት አንተ ነህ ስለ ዓለሙ መዳን ነውር የሌለበት መስዋዕት እንድትሆን መናገርን አስቀደምህ። አሁንም ከበጎነትህ ቸርነት እንለምናለን

which did come down from heaven, and foretell that Thou wouldest be the Lamb without Spot for the life of the world:

እንማልዳለንም ሰው ወዳጅ ሆይ ያንተ በሚሆን በዚህ በመንፈሳዊ ታቦት ላይ ባኖርነው በዚህ ኅብስት ላይና በዚህ ጽዋ ላይ ፊትህን ግለፅ። ይህንን ኅብስት ባርከው፤ ይህንንም ጽዋ አክብረው ሁለቱንም አንጻቸው።

We now pray and beseech of Thine excellent goodness, O lover of man, make Thy face to shine upon this bread, and upon this cup, which we have set upon this spiritual ark of Thine: Bless this bread, and hallow this cup, and cleanse them both.

ይህ ንጹሕ ሥጋህን ይሆን ዘንድ ለውጠው።
በዚህ ጽዋ ውስጥ የተቀዳውም ወይን የከበረ
ደምህን ይሁን፤ ለሁላችንም ያረገ ለነፍሳችንና
ለሥጋችን ለልቡናችንም ፈውስ ይሆን ዘንድ።

And change this bread to become. Thy pure body, and what is mingled in this cup to become Thy precious blood, let them be offered for us all for healing and for the salvation of our soul and our body and our spirit.

አምላካችን ክርስቶስ የሁላችን ንጉሥ አንተ ነህ። ከፍ ያለ ምስጋናንና ክብርን ስግደትንም ላንተ እንልካለን። ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባትህ ጋራ ከአንተ ጋራ ከሚተካከል ከማሕየዊ መንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ፤ አሜን።

Thou art the King of us all, Christ our God, and to Thee we send up high praise and glory and worship, with Thy good heavenly Father and the Holy Spirit, the life giver, who is co-equal with Thee, both now and ever and world without end. Amen.

ዲያቆን

ትእዛዘ አበዊነ ሐዋርያት ኢያንብር ብእሲ ውስተ ልቡ ቂመ ወበቀለ ወቅንዓተ ወጽልአ ላዕለ ቢጹ ወኢላዕለ መኑሂ።

ይህ የአባቶቻችን የሐዋርያት ትእዛዝ ነው። ሰው በልቦናው ቂምንና በቀልን ቅንዓትንና ጠብን በባልን ጀራው ላይ በማንም ላይ ቢሆን አይያዝ።

This is the order of our fathers the Apostles: Let none Keep in his heart malice or revenge or envy or hatred towards his neighbor, or towards any other body.

ዲያቆን

ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት

በፍርሃት ሁናችሁ ለእግዚአብሔር ስገዱ

Worship the Lord with fear.

ሕዝብ

ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ

አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን እናመሰግንሃለንም

Before Thee, Lord, we worship, and Thee do we glorify.

ፍትሐ ዘወልደ - *“The Absolution of the Son”*

አቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ ዋሕድ የእግዚአብሔር አብ ቃል ማሕየዊት መድኃኒትም በምትሆን በሕማምህ ከእኛ የኃጢአታችንን ሁሉ ማሰሪያ ያጠፋህ። ን ጹሐን አገልጋዮችህ ፊት እፍ ያልህባቸዉ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ፤ ይቅር ላላችኋቸዉ ኃጢአታቸዉ ይቀርለቸዋል ፤ ይቅርም ላላላችኋቸዉ ኃጢአታቸዉ አይቀርለቸዉም ያልካቸዉ

Master, Lord Jesus Christ, the only-begotten Son, the Word of God the Father, Who has broken off from us all the bonds of our sins through Thy life-giving and saving sufferings, Who breathed upon the face of Thy holy disciples and pure ministers saying to them : “Receive the Holy Spirit_ whatsoever of men’s sins you remit they are remitted unto them, and whatsoever sins you retain they are retained.”

አሁንም በክብርት ቤተ ክርስቲያንህ ሁልጊዜ
የክህነትን ሥራ ለሚሰሩ ለንጹሓን አገልጋዮችህ
አቤቱ አንተ ክህነትን ሰጠህ ፤ በምድር ላይ
ኃጢአትን ይቅር ይሉ ዘንድ። ያስሩ ዘንድ የበደልን
ም ማሰሪያ ሁሉ ይፈቱ ዘንድ።

Thou therefore, O Lord, has now granted the priesthood to Thy pure ministers who always do the priests' office in Thy holy church that they may remit sin on earth, may bind and loosen all the bonds of iniquity.

አሁንም አቤቱ ሰዉ ወዳጅ ሆይ ፤ ዳግመኛ ከቸርነትህ እን ለምናለን እንሻለንም። ስለነዚህ ስለ ወዳጆችም ስለ ሴቶችም ባሮችህ ፤ አባቶቼና ወንድሞቼ እኅቶቼም ደካማ ስለምሆን ስለ እኔም ስለ ባርያህ ፤ በቅዱስ መሠዊያህም ፊት ራሳቸዉን ዝቅ ስለ አደረጉ ሰዎች የምሕረትህን ጎዳና ጥረግልን የኃጢአታችንን ማሰሪያም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋልን

Once again we pray and en-treat of Thy goodness, O lover of man, on behalf of these Thy servants and handmaids, my fathers and my brothers and my sisters, and also on my own behalf, on me thy feeble servant, and on behalf of them that bow their heads before Thy holy altar. Prepare for us the way of Thy mercy, break and sever all the bonds of our sins

አቤቱ አንተን ብንበድል በማወቅ ወይም ባለማወቅ በተን ኮልም ቢሆን በልቡና ክፋትም ቢሆን በመሥራትም ቢሆን በመናገርም ቢሆን የሰዉን ድካሙን አንተ ታዉቃለህና። ቸር ሰዉ ወዳጅ ሆይ የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ አቤቱ የኃጢአታችንን ሥርየት ስጠን ፤ ባርከን ፤ አክብረንም ነጻም አድርገን ፤ አን ጻን የተፈታን ነጻም የወጣን አድርገን ሕዝቡንም ሁሉ ፍታቸዉ

whether we have tres-passed against Thee, O Lord, wittingly or unwittingly, whether in deceit or in vileness of heart, whether in deed or in word or through limited understanding, for Thou knows the feebleness of man. O good lover of man and Lord of all creation, grant us, O Lord, forgiveness of our sins, bless us and purify us, set us free and absolve all Thy people

ስምህን መፍራትንም የተመለን አድርገን። ቅዱስ ፈቃድህንም በመፍራት አጽናን። ቸር ሆይ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን አንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ነህና። ምስጋናንና ክብርን ለአንተ እናቀርባለን። ሰማያዊ ከሚሆን ከቸር አባትህ ጋራ ፤ ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ትክክል የሚሆን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

and fill us with the fear of Thy name, and confirm us in doing Thy will. O Good One, for Thou art our Lord, God, and Saviour Jesus Christ, to Thee we send glory and honour, with the good heavenly Father, and the life–giving Holy Spirit, Who is coequal with Thee, both now and ever and unto the ages of ages. Amen

በዚህች ቀን ያገለገሉህ ባሮችህ ቅሱና ዲያቆኑ ካህናቱም ሕዝቡም ሁሉ እኔም ድኃዉ ባርያህ የተፈቱና ነጻ የወጡ የነጹ ይሁኑ። ልዩ ሦስት በሚሆን በአብ በወልድ በምንፈስ ቅዱስ አፍ ሐዋርያት በሰበሰቧት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን አፍ ፤ በዓሥራ አምስቱ ነቢያት አፍ በዓሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አፍ ፤ ሥልጣን

May thy servants who serve on this day, the priests, deacons and other clergy *(+ over the clergy)*, and all Thy people *(+ over the people)*, and I myself *(+ over himself),*be absolved and set free, cleansed out of the mouth of the Holy Trinity: the Father, Son, and Holy Spirit, and out of the mouth of the one holy apostolic church, and out of the mouths of the fifteen prophets, and out of the mouths of the twelve apostles,

አገልጋዮች በሆኑ በሰባ ሁለቱ አርድዕት አፍ መለኮትን በተናገረ መንፈሳዊ ሐዋርያና አማእትም በሆነ በማርቆስ አፍ። ንጹሕ ክቡር አባት በሚሆን በጳጳሳቱ አለቃ በሳዊሮስና በቅዱስ ዲዮስቆሮስ በቅዱስ አትናቴዎስም በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና በቅዱስ ቄርሎስ በቅዱስ ጎርጎርዮስና በቅዱስ ባስልዮስ ቃል።

and out of the mouths of the seventy-two disciples and ministers, and out of the mouth of the speaker of divinity, the evangelist Mark, the apostle and martyr: and out of the mouths of the Patriarchs St. Severus, St. Dioscorus, St. Athanasius, St. John Chrysostom, St. Cyril, and Saints Gregory and Basil :

አርዮስን ለማዉገዝ በኒቅያ በተሰበሰቡ ሃይማኖታቸዉ በቀና በሦስት መቶ ዐሥራ ሰምንት ሊቃዉንትም ቃል። መቅዶንዮስን ለማዉገዝ በቁስጥንጥንያ በተሰበሰቡ በመቶ አምሳዉ ሊቃዉንትም ቃል ንስጥሮስን ለማዉገዝ በኤፌሶን በተሰበሰቡ በሁለት መቶ ሊቃዉንትም ቃል በክቡር የጳጳሳቱ አለቃ . . . . . .

and out of the mouths of the 318 orthodox that assembled in Nicaea to condemn Arius, and out out the mouths of the 150 that assembled in Constantinople to condemn Mace-donius, and out of the mouths of the 200 that assembled in Ephesus to condemn Nestor, and out of the mouth of the honoured Patriarch Abba . . . . . .

ንዑድ ክቡር በሚሆን በጳጳሳችን በአባ . . . . . ቃል ድኃ ምስኪን በምሆን በኔም በኃጥኡ ቃል የተፈቱ ነጻም የወጡ ይሁኑ። አምላክን በወለደች በሁለት ወገን ድንግል በሆነች ባዲሲቱ መሣሪያ በክብርት እመቤታችን በማርያም ቃል። የቅዱስ ስምህ ምስጋና ቡሩክ ፍጹም ነዉና ፤ ልዩ ሦስት የምትሆን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ፤ አሜን።

and the blessed Archbishop Abba (____), and out of the mouth of me also the sinful, miserable, and poor: may they be absolved and set free, and out of the mouth of our Lady holy Mary, of twofold vir-ginity, Mother of God, the new loom.

For Thy holy name is blessed and full of glory, O holy Trinity, Father, Son, and Holy Spirit, both now and ever and unto endless ages. Amen.

ዲያቆኑ ሲጸልይ ሕዝቡ በመከተል በየምዕራፉ
«አሜን ኪርየላይሶን አቤቱ ይቅር በለን» ይበል

<u>ዲያቆን</u>

አንድ ስለምታደርግ ሥጋውና ደሙ
እግዚአብሔር በይቅርታው አንድ ያደርገን
ዘንድ ሰላምን እንማልዳለን።

For the peace holy things we beseech, that God may grant us peace through His Mercy.

እግዚአብሔር የሱን ሃይማኖት በንጹሕ እንድንጠብቅ ይሰጠን ዘንድ ስለ ሃይማኖታችን እንማልዳለን

For our Faith we beseech, that God may grantus to keep the faith in purity.

እስከ ፍጻሜያችን ድረስ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አን ድነት ይጠብቀን ዘንድ ስለ አንድነታችን እንማልዳለን

For our congregation we beseech, that God may keepus unto the end in the communion of the Holy Spirit.

በመከራችን ሁሉ እግዚአብሔር የትዕግሥትን ፍጻሜ ይሰጠን ዘንድ ስለ ነፍሳችን ትዕግሥት እንማልዳለን

For patience of soul we beseech, that God may vouchsafe us perfect patience in all our tribulation

ቅዱሳን ስለሚሆኑ ነቢያት ከሳቸው ጋራ እግዚአብሔር ይቈጥረን ዘንድ እንማልዳለን

For the holy prophets we beseech, that God may number us with them.

እነሱ ደስ እንዳሰኙት ደስ ልናሰኘው እግዚአብሔር (ማገልገሉን) ይሰጠን ዘንድ ዕድል ፈንታቸውንም ያድለን ዘንድ አገልጋዮች ስለሚሆኑ ሐዋርያት እንማልዳለን

For the ministering Apostles we beseech, that God may grant us to be well pleasing even as they were well pleasing, apportion unto us a lot with them.

እግዚአብሔር ለኛ የሰማዕትነትን ሥራ ይሰጠን ዘንድ ቅዱሳን ስለሚሆኑ ሰማዕታት እንማልዳለን

For the Holy martyrs we beseech, that God may grant us to perfect the same conversation.

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እነሱ ናቸውና እግዚአብሔር እነሱን ለረጅም ወራት ይሰጠን ዘንድ ያለ ነውር በንጽሕና ሆነው በዕውቀት የሃይማኖትን ቃል ያቀኑ ዘንድ ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ . . . . ብጹዕ ስለሚሆን ስለ ሊቀ ጳጳሳችንም አባ . . . እንማልዳለን

For our Patriarch … and the blessed Archbishop … we beseech, that grant them length of days to be over us, that with understanding they may rightly speak the word of faith in purity without spot for that they are the defenders of the church.

የክህነትን ሥልጣን ከእነሱ እግዚአብሔር እንዳያርቅ መትጋትን እሱን መፍራትንም እስከ ፍጻሜ ይሰጥልን ዘንድ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ስለ ቀሳውስት እንማልዳለን

For the priests we beseech, that God may never take from them the spirit of priesthood, and may give them the grace of zeal and fear of Him unto the end and accept their labor.

ፈጽመው ሊፋጠኑ መፋጠንን እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ በቅድስናም ይቀርቡ ዘንድ ድካማቸውንና ፍቅራቸውንም ያስብ ዘንድ ስለ ዲያቆናት እንማልዳለን

For the deacons we beseech, that God may grant them to run a perfect course, and draw them high unto Him in holiness, and remember their labor and their love.

የሃይማኖታቸውን ትጋት ሊፈጽሙ እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ስለ ንፍቀ ዲያቆናት ስለ አንባቢዎችም ስለ መዘምራንም እንማልዳለን

For the assistant deacons and the anagnosts and the singers we beseech, that God grant them to perfect the diligence of their faith.

ልመናቸውን ይሰማቸው ዘንድ ይልቁንም የመንፈስ ቅዱስን ሀብት በልቡናቸው ያሳድርባቸው ዘንድ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ስለ ባልቴቶች ረዳትም ስለሌላቸው እንማልዳለን

For the widows and the bereaved we beseech, that God may hear their prayers and vouchsafe them abundantly in their hearts the grace of the Holy Spirit and accept their labor.

እግዚአብሔር የድንግልናቸውን ዋጋ (አክሊል) ይሰጣቸው ዘንድ ለእግዚአብሔርም ወንዶችም ሴቶች ልጆች ይሆኑት ዘንድ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ስለ ደናግል እንማልዳለን

For the virgins we beseech, that God may grant them the crown of virginity, and that they may be unto God sons and daughters and that He may accept their labor.

በመታገሳቸው ዋጋቸውን ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው ስለሚታገሱ ሰዎች እንማልዳለን

For those who suffer patiently we beseech, that God grant them to receive their rewards through patience.

በንጽሕና ሆነው ይጠብቁ ዘንድ እግዚአብሔር ሃይማኖትን እንዲሰጣቸው ስለ ሕዝባውያንና ስለ መሃይምናን እንማልዳለን

For the laity and faithful we beseech, that God may grant them complete faith which they may keep in purity.

በጎውን ዕድል ታጢአትን ለማስተሰረይ ሁለተኛ መወለድ የሚገኝበትን ሕጽበት እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ በቅድስት ሥላሴም ማኅተም ያከብራቸው ያትማቸው ዘንድ ስለ ንዑሰ ክርስቲያን እንማልዳለን

For the catechumens we beseech, that God may grant them a good portion and the washing of regeneration for the remission of sin, and seal them with the seal of the Holy Trinity.

በዘመኑ ፍጹም ሰላምን እግዚአብሔር ይሰጣት ዘንድ እግዚአብሔርን ስለምትወድ ስለ አገራችን ኢትዮጵያ እንማልዳለን

For our country Ethiopia we beseech, that God may give her peace forever.

ዕውቀትን እሱን መፍራትንም እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ስለ መኳንንትና ሥልጣን ስላላቸው እንማልዳለን

For the rulers and those in authority we beseech, that God may grant them of His wisdom and His fear.

ስለዓለሙ ሁሉ እግዚአብሔር ማሰብን
ያስቀድም ዘንድ ለእያንዳንዱም
የሚያስፈልገውን ያማረውን የሚሻውንም ያስብ
ዘንድ ስለ ዓለም ሁሉ እንማልዳለን

For the whole world we beseech, that God should hasten His purpose and put into the mind of all and each to desire that which is good and expedient.

እግዚአብሔር ይቅርታ ባለው ቀኝ መርቶ በፍቅርና በደኅንነት ወደ ማደሪያቸው ይመልሳቸው ዘንድ በባሕርና በደረቅ ስለሚሄዱ ሰዎች እንማልዳለን

For them that travel by sea and by land we beseech, that God should guide them with a merciful right hand and let them enter their home in safety and peace.

እግዚአብሔር የዕለት የዕለት ምግባቸውን ይሰጣቸው ዘንድ ስለተራቡና ስለተጠሙ ሰዎች እንማልዳለን

For the hungry and the thirsty we beseech, that God should grant them their daily food.

እግዚአብሔር ፈጽሞ ያረጋጋቸው ዘንድ ስለ አዘኑና ስለተከዙ ሰዎች እንማልዳለን

For the sad and the sorrowful we beseech, that God may give them perfect consolation.

እግዚአብሔር ከእሥራታቸው ይፈታቸው ዘንድ ስለ ታሠሩ ሰዎች እንማልዳለን

For the prisoners we beseech, that God may loose them from their bonds.

እግዚአብሔር በሰላም ወደ አገራቸው ይመልሳቸው ዘንድ ስለተማረኩ ሰዎች እንማልዳለን

For the captives we beseech, that God may restore them to their county in peace.

እግዚአብሔር ትዕግሥትን በጎ ትምህርትንም ይሰጣቸው ዘንድ የድካማቸውንም ፍጹም ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ ስለተሰደዱ ሰዎች እንማልዳለን

For those who were sent away we beseech, that God should grant them patience and good instruction, and give them complete reward for their labor.

እግዚአብሔር ፈጥኖ ያድናቸው ዘንድ ይቅርታውንና ቸርነቱንም ይልክለቸው ዘንድ ስለታመሙትና ስለድውያኑ እንማልዳለን

For the sick and the diseased we beseech, that God should heal them speedily and send upon them mercy and compassion.

ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወገን ስለ ሞቱ ሰዎች እግዚአብሔር የዕረፍት ቦታ ይሰጣቸው ዘንድ እን ማልዳለን

For those who have fallen asleep in his holy church we beseech, that God may vouchsafe them a place to rest.

እግዚአብሔር እንዳይቀየማቸው ከመዓትም ተመልሶ ፍጹም ዕረፍትን ይሰጣቸው ዘንድ ስለ በደሉ አባቶቻንናወንድሞቻችን እንማልዳለን

For those who have sinned, our fathers and our brothers we beseech, that God cherish not anger against them, but grant them rest and relief from His wrath.

በሚሻበት ቦታ እግዚአብሔር ዝናቡን ያዘንብ ዘንድ ስለ ዝናብ እንማልዳለን

For the rains we beseech, that God may send rain on the place that needs it.

የወንዙን ውኃ ሙላልን ብለን እግዚአብሔር እነሱን እሰከ ልካቸውና እሰከ መሰናቸው ይሞላ ዘንድ ስለ ወንዝ ውኃ እንማልዳለን

For the water of the rivers we beseech, that God should fill them unto their due measure and bounds

ለዘርና ለመከር ሊሆን እግዚአብሔር ለምድር ፍሬዋን
ይሰጣት ዘንድ ስለ ምድር ፍሬ እንማልዳለን

For the fruits of the earth we beseech, that God may grant to the earth her fruit for sowing and for harvest.

በጸሎት የምንለምንና የምንማልድ ሁላችንንም በሰላም
በመንፈስ ይጠብቀን ፤ ፍቅርንም ይስጠን ዓይነ
ልቡናችንንም ያብራልን ፤ ፈቃዱም ሆኖ ጸሎታችንን
ይቀበል ዘንድ ቀርበን እግዚአብሔርን እንለምነው

And all of us who ask and beseech in prayer, may He cover us with the spirit of peace, and give us grace, and enlighten the eyes of our hearts. Let us draw high and ask God to accept our prayers according to His will.

አውቀን በሀብቱ እናድግ ዘንድ በእርሱም ስም እን
መካ ዘንድ በነቢያት በሐዋርያትም መሠረት ላይ እን
ታነፅ ዘንድ እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ እንነሣ ቀርበን
አምላካችን እግዚአብሔርን እንለምነው ወደ
ጸሎታችንን ይቀበል ዘንድ

Let us therefore rise in the Holy Spirit, growing in His grace, with understanding, glorying in His name and built upon the foundation of the prophets and the apostles. Let us draw high and ask Lord God to accept our prayers according to His will.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለን

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ካህን

ንስግድ (3 ጊዜ)

እንስገድ (3 ጊዜ)

Let's worship (to be repeated thrice)

ሕዝብ

ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ
ሠለስቱ አሐዱ (3 ጊዜ)

ሦስት ሲሆኑ አንድ ለሚሆኑ ለአብና
ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም (3 ጊዜ)

The Father and the Son and the Holy Spirit, three in one. (to be repeated thrice)

ካህን

ሰላም ለኪ

ሰላምታ ይገባሻል

Peace be unto thee:

ሕዝብ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማኅደረ መለኮት

የመለኮት ማደሪያ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

Holy church, dwelling-place of the Godhead.

ካህን

ሰአሊ ለን

ለምኝልን

Ask for us:

ሕዝብ

ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ

አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም

Virgin Mary, mother of God,

ካህን

አንቲ ውእቱ

አንቺ ነሽ

Thou art:

ሕዝብ

ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ፆርኪ ፍሕመ እሳት
ቡሩክ ዘነሥዓ እመቅደስ ዘይሠሪ ኃጢአተ
ወይደመስስ

ቡሩክ ከቤተ መቅደስ የተቀበለት የእሣትን
ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ጥና አንቺ ነሽ ፤

the golden censer which didst bear the coal of fire which the blessed took from the sanctuary,

ጌጋየ ዝውእቱ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ
እምኔከ ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ ወመሥዋእተ

ኃጢአትን የሚያስተሰርይ በደልንም የሚያጠፋ
ይኸውም ካንቺ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው

and which forgiveth sin and blotteth out error, who is God's Word that was made man from thee, who offered Himself to his Father for incense and an acceptable sacrifice.

ሥሙረ። ንሰግድ ለከ ክርስቶስ ምስለ አቡከ
ኄር ሰማያዊ ወመንፈስከ ቅዱስ ማሕየዊ
እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ።

ክርስቶስ ሆይ ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባትህ
ጋራ መድኃኒት ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ
እንሰግድልሃለን መጥተህ አድኸናልና።

We worship Thee, Christ, with thy good heavenly Father and thy Holy Spirit, the life-giver, for Thou didst come and save us.

ካህን

ተዘከር እግዚኦ ለአቡነ . . . ዕቀቦ ዓመታት ብዙኀ መመዋዕለ ነዊኀ በጽድቅ ወበሰላም። አግርር ፀሮ ታሕታ እገሪሁ የሰአል ለነ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

አባታችንን . . . አስበው። ረጅም ወራት ብዙ ዘመን በውነትና በፍቅር ጠብቀው። ጠላቶቹን ከእግሩ በታች አስገዛለት ኃጢአታችንንሊያስተሠርይልን ወደ እግዚአብሔር ይለምን ዘንድ።

Remember our father, the blessed . . . Patriarch Keep him for many years and length of days in righteousness and peace. Subject his enemies under his feet so that he may pray for us to God, that He may forgive us our sins.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለን

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

(በመቀባበል ይደገማል)

ካህን ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ

ዲ/ህ ይደልዎሙ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ካህን አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኩሎ ጊዜ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም

ሕዝብ አሜን

ልዩ ሦስት ለሚሆን ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ሁልጊዜ ክብር ምስጋና ይገባቸዋል ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን

Glory and honor are meet to he Holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit at all times. Both now and ever and world without end. Amen

ዲያቆን - ኩሉ ዘኢ.ያፈቅሮ ለእግዚእነ መመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ መዘኢየአምን ልደቶ እማርያም እምቅድስት ድንግል በፀኤ ታቦተ መንፈስ ቅዱስ እስከ ምጽአቱ ሐዳስ በከመ ይቤ ጳውሎስ ውጉዘ ለይኩን።

ጌታችንንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወደው የመን ፈስ ቅዱስ ማደሪያ በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከቅድስት ማርያም መወለዱንም የማያምን ሰው ሁሉ እንግዳ እስከሚሆን ምጽአቱ ድረስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ የተለየ ይሁን።

Every one that loves not our Lord and our Saviour Jesus Christ, and believes not in his birth from holy Mary, of twofold virginity, the ark of the Holy Spirit, until His coming again, let him be anathema as Paul said.

የሐዋርያው የጳውሎስ መልዕክት ወደ

ሕዝብ

ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሠናየ መልእክት ፈዋሴ ዱያን ዘነሳእከ አክሊለ ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ ያድኅን ነፍሳተነ በብዝኃ ሣህሉ ወምሕረቱ በእንተ ስሙ ቅዱስ

አክሊለ ሰማዕታትን የተቀበልህ ድውያንን የምታድን መልእክትህ የበጀ ክቡር የምትሆን ጳውሎስ ሆይ ስለእኛ ለምንልን በይቅርታው ቸርነቱ ብዛት ሰውነታችንን ይድን ዘንድ በክብር ስሙ ስለአመንን

Holy Apostle Paul, good messenger, healer of the sick, who hast received the crown, ask and pray for us in order that he may save our souls in the multitude of his mercies and in his pity for his holy name's sake.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ዲያቆን

ነገር ዘእመልእክተ ..... ረድኡ ወሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ኩልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያው ረድኡ ከሚሆን መልእክት የተገኘ ቃል ይህ ነው ጸሎቱ በረከቱ በሕዝበ ክርስቲያኑ ይኑር ለዘላለሙ አሜን።

The word from the Epistle of the disciple and apostle of our Lord Jesus Christ, _____, may his prayer and blessing be on our fellow Christians for ever. Amen.

2ኛ መልዕክት

ሕዝብ

ቅዱስ ሥሉስ ዘኅቡር ህላዌከ ዕቀብ ማኅበረነ በእንተ ቅዱሳን ኅሩያን አርዳኢከ ናዝዘነ በሣህልከ በእንተ ቅዱስ ስምከ።

ባሕርይህ አንድ የሚሆን ልዩ ሦስት ሆይ አንድነታችንን ጠብቅ ስለ ተመረጡ ክቡራን ደቀ መዛሙርትህ በይቅርታህ አጽናን ክቡር ስለሚሆን ስለ ስምህ ብለህ።

Holy con substantial Trinity, preserve our congregation for Thy holy elect disciples' sake: comfort us in Thee mercy, for Thy holy name's sake.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለን

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ካህን

ነቅሕ ንጹሕ ዘእምአንቅዕተ ሕግ ንጹሓን ዝውእቱ ዜና ግብሮሙ ለሐዋርያት በረከተ ጸሎቶሙ የሀሉ ምስለ ኩልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን።

ንጹሓን ከሚሆኑ ከሕግ ምንጮች የተገኘ ጥሩ ምንጭ ይኸውም የሐዋርያት የሥራቸው ነገር ነው የጸሎታቸው በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

A pure fountain which is from the pure fountains of the law, to wit the history of the acts of the apostles. The blessing of their prayer be with our people for ever. Amen.

ግብረ ሐዋርያት

የሐዋርያት ሥራ

ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ አብ
አጋዜ ኩሉ።

ሁሉን የያዝህ አብ ሆይ ቅዱስ
ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ።

Holy Holy Holy art Thou, Holy Father, who owns everything.

ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ወልድ ዋሕድ
ዘአንተ ቃለ አብ ሕያው

ሕያው የአብ ቃል የምትሆን ወልድ ዋሕድ
ሆይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ

Holy Holy Holy art Thou, only-begotten
Son, who art the Word of the living Father.

ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ መንፈስ ቅዱስ
ዘተአምር ኩሎ

ሁሉን የምታውቅ መንፈስ ቅዱስ ሆይ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ።

Holy Holy Holy art Thou, Holy Spirit
who knows all things.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለን

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ካህን

ደኅንነትን የምንለምንሽ ክብርን የተሞላሽ
ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ። ሁልጊዜ ድንግል

Rejoice, O thou of whom we ask healing,
O holy full of honor.

ሕዝብ

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

የምትሆኝ አምላክን የወለድሽ የክርስቶስ እናት ሆይ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ወደ ልጅሽ ወደ ወዳጅሽ ወደ ላይ ጸሎታችንን አሳርጊ።

Ever-Virgin, parent of God, mother of Christ, offer up our prayer on high to thy beloved Son that He may forgive us our sin.

ሕዝብ

አሜን

Amen.

ካህን

በእውነት የፅድቅ ብርሃን የሚሆን
አምላካችንን ክርስቶስን የወለድሽልን
(ንጽሕት) ሆይ ደስ ይበልሽ

Rejoice, O thou who didst bear for us the very light of righteousness, even Christ our God.

ሕዝብ

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

ንጽሕት ድንግል ሆይ ለነፍሳችን ይቅርታን ያደርግ ዘንድ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ ወደ ጌታችን ለምኝልን ።

O Virgin pure, plead for us unto our Lord that He may have mercy upon our souls and forgive us our sin.

ሕዝብ

አሜን

Amen.

ካህን

በእውነት ለሰው ወገን አማላጅ የምትሆኝ ፤
አምላክን የወለድሽ ንጽሕት ቅድስት
ድንግል ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ።

Rejoice, O Virgin Mary, parent of God, holy and pure, very pleader for the race of mankind.

ሕዝብ

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

የኃጢአታችንን ሥርየት ይሰጠን ዘንድ
በልጅሽ በክርስቶስ ፊት ለምኝልን።

Plead for us before Christ thy Son, that He may vouchsafe us remission of our sins.

ሕዝብ

አሜን

Amen.

ካህን

በእውነት ንግሥት የምትሆኝ ንጽሕት ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ

Rejoice, O Virgin pure, very Queen.

ሕዝብ:- ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

የባሕርያችን መመኪያ ሆይ ደስ ይበልሽ

Rejoice, O pride of our kind.

ሕዝብ:- ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

አምላካችን አማኑኤልን የወለድሽልን ሆይ
ደስ ይበልሽ

Rejoice, O thou that barest for us Emmanuel our God.

ሕዝብ

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እውነተኛ አስታራቂ ሆነሽ ታስቢን ዘንድ እንለምንሻለን ለነፍሳችን ይቅርታን ያደርግልን ዘንድ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ

We ask thee to remember us, O true Mediatrix, before our Lord Jesus Christ that He may have mercy upon our souls and forgive us our sins.

ሕዝብ:- አሜን

Amen.

ካህናት

ዝውእቱ ጊዜ ባርኮት ወዝ ውእቱ ጊዜ
ዕጣን ኅሩይ ጊዜ ሰብሐቱ ለመድኃኒነ
መፍቀሬ ሰብእ ክርስቶስ።

የማመስገን ጊዜ ይህ ነው።የተመረጠ
የዕጣን ጊዜም ይህ ነው። ሰውን ወዳጅ
መድኃኒታችንን ክርስቶስን ማመስገኛ ጊዜ።

This is the time of blessing; this is the time of chosen incense, the time of the praise of our Savior, lover of man, Christ.

ሕዝብ

ዕጣን ይእቲ ማርያም ዕጣን ውእቱ እስመ ዘውስተ ከርሣ ዘይትዐዝ እምኩሉ ዕጣን ዘወለደቶ መጽአ ወአድኀነነ

ማርያም ዕጣን ናት ፤ ዕጣን እርሱ ነው።
በማኅጸንዋ ያደረው ከተመረጠ ዕጣን ሁሉ
የሚሸት ነውና ፤ የወለደችው መጥቶ አዳነን

Mary is the incense, and the incense is He, because he who was in her womb is more fragrant than all chosen incense. He whom she bare came and saved us.

ካህናት

ዕፍረት ምዑዝ ኢየሱስ ክርስቶስ ንዑ ንስግድ ሎቱ ወንዕቀብ ትእዛዛቲሁ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

ኢየሱስ ክርስቶስ መዓዛ ያለው ሽቱ ነው ፤ ኑ እንስገድለት ትእዛዞቹንም እንጠብቅ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ።

The fragrant ointment is Jesus Chris. O! come let us worship Him and keep His commandments that He may forgive us our sins.

ሕዝብ

ተውህቦ ምሕረት ለሚካኤል ወብሥራት ለገብርኤል
ወሀብተ ሰማያት ለማርያም ድንግል

ለሚካኤል ምሕረት ተሰጠው ለገብርኤልም
ማብሠር ፤ ለድንግል ማርያም ሰማያዊ ሀብት።

To Michael was given mercy, and glad tidings to Gabriel, and a heavenly gift to the Virgin Mary.

ካህናት

ተውህቦ ልቡና ለዳዊት ወጥበብ ለሰሎሞን
ወቀርነ ቅብዕ ለሳሙኤል እስመ ውእቱ
ዘይቀብዕ ነገሥተ።

ለዳዊት ልቡና ለሰሎሞንም ጥበብ
ለሳሙኤልም ነገሥታቱን የቀባ እርሱ ነውና
የሸቱ ቀንድ ተሰጠው።

To David was given understanding, and wisdom to Solomon, and an horn of oil to Samuel for he was the anointer of kings.

ሕዝብ

ተውህቦ መራኁት ለአቡነ ጴጥሮስ ወድንግልና ለዮሐንስ ወመልእክት ለአቡነ ጳውሎስ እሰመ ውእቱ ብርሃና ለቤተ ክርስቲያን።

ለአባታችን ለጴጥሮስ መክፈቻ ለዮሐንስም ድንግልና ለአባታችን ለጳውሎስም የቤተ ክርስቲያን ብርሃኑ እርሱ ነውና መልእክት ተሰጠው።

To our father Peter were given the keys, and virginity to John, and apostleship to our father Paul, for he was the light of the church.

ካህናት

ዕፍረት ምዕዝት ይእቲ ማርያም እስመ ዘውስተ ከርሣ ዘይትሌዐል እምኩሉ ዕጣን መጽአ ወተሠገወ እምኔሃ።

መዓዛ ያላት ሽቱ ማርያም ናት ፤ በማኅጸንዋ ያለው ከዕጣን ሁሉ የሚበልጥ ነውና መጥቶ ከእርስዋ ሰው ሆነ።

The fragrant ointment is Mary, for he that was in her womb, who is more fragrant than all incense, came and was incarnate of her.

ሕዝብ

ለማርያም ድንግል ንጽሕት ሠምራ አብ
ወአሠርገዋ ደብተራ ለማኅደረ ፍቁር ወልዱ።

ንጽሕት ድንግል ማርያምን አብ ወደዳት
ለተወደደ ልጁም ማደሪያ ልትሆን አስጌጣት።

In Mary virgin pure the Father was well-pleased, and he decked her to be a tabernacle for the habitation of his beloved Son.

ካህናት

ተውህቦ ሕግ ለሙሴ ወክህነት ለአሮን ተውህቦ ዕጣን ዓሩይ ለዘካርያስ ካህን።

ለሙሴ ሕግ ለአሮንም ኽህነት ተሰጠው።
ለካህኑ ለዘካርያስም የተመረጠ ዕጣን ተሰጠው

To Moses was given the law, and priesthood to Aaron. To Zacharias the priest was given chosen incense.

ሕዝብ

ደብተራ ስምዕ ገብርዋ በከመ ነገረ እግዚእ
ወአሮን ካህን በማእከለ ያዐርግ ዕጣነ ሳሩየ።

የምስክር ድንኳን አደረጓት። ጌታ እንደተናገረ
ካህኑ አሮንም በመካከላቸው የተመረጠው ዕጣን
ያሳርጋል።

They made a tabernacle of testimony according to the word of God; and Aaron the priest, in the midst thereof, made the chosen incense to go up.

ካህናት

ሱራፌል ይሰግዱ ሎቱ ወኪሩቤል ይሴብሕዎ
ይጸርሑ እንዘ ይብሉ።

ሱራፌል ይሰግዱለታል ኪሩቤልም
ያመሰግኑታል። እንዲህ እያሉ ይዘምራሉ።

The seraphim worship him, and cherubim praise him and cry saying:

ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በጎበ አእላፍ
ወክቡር በውስተ ረበዋት።

እግዚአብሔር በአእላፍ መላእክት ዘንድ ቅዱስ
ቅዱስ ቅዱስ ነው። በአለቆችም
ዘንድ ክቡር ነው።

Holy Holy Holy is the Lord among the thousands
and honored among the tens of thousands.

በጎብረት

አንተ ውእቱ ዕጣን ኦ መድኃኒነ እስመ መጻእከ ወአድኃንከነ ተሣሃለነ።

መድኃኒታችን ሆይ! ዕጣን አንተ ነህ ፤ መጥተህ አድነኸናልና ይቅር በለን።

Thou art the incense, O our savior, for Thou didst come and save us. Have mercy upon us.

ካህን/Priest

ቅዱስ / Holy

ሕዝብ/People

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው
ዘኢይመውት ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት
ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው
የማይሞት ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ ፥
አቤቱ ይቅር በለን።

God, holy Mighty, holy Living, Immortal, who was born from the holy Virgin Mary, have mercy upon us, Lord.

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢ,ይመውት ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት በዮርዳኖስ የተጠመቀ በመስቀል ላይ የተሰቀለ ፥ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, Holy Living, Immortal, who was baptized in Jordan and crucified on the tree of the cross, have mercy upon us, Lord.

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተንሥአ እመ ኃን አመ ሣልስት

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት በሦስተኛው ቀን ከመ ኃን ተለይቶ የተነሣ

Holy God, holy Mighty, holy Living, Immortal, who didst rise from the dead on the third day,

ዕለት ወርገ በሰብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ
በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በሰብሐት
ይኵንን ሕያዋነ ወሙታነ ፤ ተሣሃለነ እግዚኦ።

በምስጋና ወደ ሰማይ ወጣ በአባቱም ቀኝ
ተቀመጠ ዳግመኛም ይመጣል በሕያዋንና
በሙታን ይፈርድ ዘንድ ፥ አቤቱ ይቅር በለን።

ascend into heaven in glory, sit at the right hand of thy Father and again wilt come in glory to judge the quick and the dead, have mercy upon us, Lord.

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት
ለመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ
ዓለም አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን።

ለአብ ምስጋና ይሁን ለወልድም ምስጋና
ይሁን ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን ዛሬም
ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን ።

Glory be to the Father, glory be to the Son, glory be to the Holy Spirit, both now and ever and world without end. Amen and Amen, so be it, so be it.

ሕዝብ/People

ቅዱስ ሥሉስ እግዚአብሔር ሕያው ተሣሃለን።

ልዩ ሦስት ሕያው እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለን።

O holy Trinity, living God have mercy upon us.

ካህን/Priest

ጸጋ ዘእግዚአብሔር የሃሉ ምስሌክሙ

የእግዚአብሔር ጸጋ ከናንተ ጋራ ይሁን

The grace of God be with you.

ሕዝብ/People

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit

ካህን/Priest

ንሰብሖ ለአምላክነ

ፈጣሪያችንን አናመስግን

Let us glory our God.

ሕዝብ/People

ርቱዕ ይደሉ

አውነት ነው ይገባል

It is right, it is just.

ካህን/Priest

አጽንዑ ሕሊና ልብክሙ

የልባችሁን አሳብ አጽኑ

Strengthen the thought of your heart.

ሕዝብ/People

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አቡነ ዘበሰማያት አቡነ ዘበሰማያት ፤ አቡነ ዘበሰማያት ፤ ኢታብአነ እግዚአ ውስተ መንሱት።

ከእግዚአብሔር ዘንድ አለን። አባታችን ሆይ አባታችን ሆይ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

We lift them unto the Lord our God. Our Father who art in heaven, Our Father who art in heaven, Our Father who art in heaven, lead us not into temptation.

ካህኑ የኪዳን ጸሎት “እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ, ……. ”
የሚለውን በንባብ ያሰማሉ

The priest will read the “O Lord, Jesus Christ”
Prayer of the Covenant.

ሕዝብ/People (ጠዋት/Morning)

ኪያከ ንሴብሕ እግዚኦ

አቤቱ አንተን እናመሰግናለን

Oh Lord, we praise Thee

ሕዝብ/People (ከሰዓት/Afternoon)

ንሴብሐከ እግዚኦ

አቤቱ አንተን እናመሰግናለን

Oh Lord, we praise Thee

ሕዝብ/People (ጠዋት/Morning)

ኪያከ ንቄድስ እግዚኦ

አቤቱ አንተን እናመሰግናለን

Oh Lord, we praise Thee

ሕዝብ/People (ከሰዓት/Afternoon)

ንቄድሰከ እግዚኦ

አቤቱ አንተን እናመሰግናለን

Oh Lord, we praise Thee

ሕዝብ/People

አሜን

Amen

ሕዝብ/People

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ . . .

አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር . . .

Our Father in Haven . . .

በሰላመ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዚእትየ . . .

አመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ. . .

Hail Mary . . .

አጋእዝተ ዓለም ሥላሴ

ሕዝብ/People

አ ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ ፤ አ ሥሉስ ቅዱስ መሐከነ ፤ አ ሥሉስ ቅዱስ ተሣሃለነ

ልዩ ሦስት ሆይ ማረን ፤ ልዩ ሦስት ሆይ ራራልን ፤ ልዩ ሦስት ሆይ ይቅር በለን

O! Holy Trinity, Pity us, O! Holy Trinity, Spare us, O! Holy Trinity, have mercy upon us.

ካህን/Priest

ተፈሥሒ ተፈሥሒ ተፈሥሒ አ
ማርያም ድንግል ምልዕተ ጸጋ።

ጸጋን የተሞላሽ ድንግል ማርያም ሆይ
ደስ ይበልሽ ደስ ይበልሽ ደስ ይበልሽ

Rejoice rejoice rejoice, O! Virgin Mary,
full of grace

ሕዝብ/People

እግዚአብሔር ምስሌኪ

እግዚአብሔር ካንቺ ጋራ ነው

The Lord is with Thee.

ካህን/Priest

ቡሩክት አንቲ እምአንስት

ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ።

Blessed art Thou among women:

ሕዝብ/People

ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ

የማሳደጉሽም ፍሬ የተባረከ ነው።

And blessed is the fruit of thy womb.

ካህን/Priest

ሰአሊ ለነ ኀበ ክርስቶስ ወልደኪ

ከልጅሽ ከክርስቶስ ዘንድ ለምኝልን።

Pray for us to Christ thy Son.

ሕዝብ/People

ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ

ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ።

To forgive us our sins.

ዲያቆን/Deacon

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ/People

እግዚኡ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን/Priest

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ/People

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ካህን/Priest

አቤቱ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀመዛሙርትህንና ንጹሐን ለሐዋርያት እንዲህ ያልሃቸው እናንተ የምታዩትን ያዩ ዘንድ ብዙ ነቢያት ጻድቃን ወደዱ አላዩም። እናንተ ዛሬ የምትሰሙትንም ይሰሙ ዘንድ ወደዱ አልሰሙም።

O Lord Jesus Christ, our God, who didst say to Thy holy disciples and Thy pure apostles: Many prophets and righteous men have desired to see the things which Ye see and have not seen them, and have desired to hear the things which Ye hear and have not heard them,

የእናንተ ያዩ ዓይኖቻችሁና የሰሙ ጆሮቻችሁ ግን የተመሰገኑ ናቸው። እኛንም እንደ እነሱ የበቃን አድርገን ፤ በቅዱሳን ጸሎት የከበረ ወንጌልን ቃል ሰምተን እንሠራ ዘንድ።

but You, blessed are Your eyes that have seen and you ears that have heard, Do Thou make us also like them meet to hear and to do the word of Thy Holy Gospel through the prayer of the saints.

ዲያቆን/Deacon

ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ።

ክቡር ስለሚሆን ወንጌል ጸልዩ።

Pray for the Holy Gospel

ሕዝብ/People

ይረስየነ ድልዋነ ለሰሚዐ ወንጌል ቅዱስ።

የከበረ ወንጌልን ለመስማት የበቃን ያድርገን።

May He make us meet to hear the Holy Gospel.

የዕለቱ ምስባክ

ዲያቆን/Deacon

ሃሌ ሉያ! ቁሙ ወአጽምዑ ወንጌለ ቅዱሰ ዜናሁ ለእግዚእነ መመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ሃሌ ሉያ! ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቅዱስ ወንጌል ቁማችሁ ስሙ።

Halleluiah, stand up and hearken to the Holy Gospel, the message of our Lord and Savior Jesus Christ.

ካህን/Priest

እግዚአብሔር ምስለ ኩልክሙ።

እግዚአብሔር አድሮባችሁ ይኑር።

The Lord be with you all.

ሕዝብ/People

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋር።

And with Thy spirit

ካህን/Priest

ወንጌል ቅዱስ ፤ ዘዜነወ ማቴዎስ/ማርቆስ/ ሉቃስ (ዘሰበከ ዮሐንስ) ቃለ ወልደ እግዚአብሔር

ማቴዎስ/ማርቆስ/ ሉቃስ/ዮሐንስ የተናገረው የእግዚአብሔር ልጅ ቃል የሚሆን ቅዱስ ወንጌል

The Holy gospel according to Matthew/ Mark/ Luke/ John the Word of the Son of God.

ሕዝብ/People

ስብሐት ለከ ክርስቶስ እግዚአየ
ወአምላኪየ ኩሎ ጊዜ

ጌታዬና አምላኬ ክርስቶስ ሆይ
ሁልጊዜ ለአንተ ምስጋና ይገባል።

Glory be to Thee, Christ my Lord and my God, at all times.

(በጸም ወራት)

በወንጌል መራኽከነ ወበነቢያት ናዘዝከነ
ዘለሊከ አቅረብከነ ስብሐት ለከ።

በወንጌል መራኽን በነቢያትም አጸናኽን አንተ
ቅሉ ላቀረብኽን ምስጋና ይገባል።

Thou has guided us with the Gospel, comforted us with the prophets, and drawn us near unto Thee. Glory be to Thee.

ተፈሥሑ በእግዚአብሔር ዘረድኣነ ወየብቡ
ለአምላከ ያዕቆብ ፤ ንሥኡ መዝሙረ ወሀቡ
ከበሮ መዝሙር ሐዋዝ ዘምስለ መሰንቆ

በረዳን በእግዚአብሔር ደስ ይበላቸሁ
የያዕቆብምንም አምላክ አመስግኑ መዝሙሩን
ያዙ ፤ ከበሮውንም ስጡ መዝሙር ከበገና ጋራ
የተስማማ ነው።

Sing aloud unto God our strength: make a joyful noise unto the God of Jacob. Take a psalm, and bring hither the timbrel, the pleasant harp with the psaltery.

ካህን/Priest

ነዋ ወንጌለ መንግሥት።

ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታገባ ወንጌል እነሆ!

Behold the Gospel of the kingdom of heaven.

ንፍቅ ካህን/Asst. priest

መንግሥቶ ወጽድቆ ዘአወፈየኒ አወፈይኩከ።

መንግሥቱንና ጽድቁን የሰጠኝን ሰጠኹኽ

His kingdom and His righteousness which he delivered to me: I deliver to you.

ዲያቆን/Deacon

ንስሑ ወአመኑ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት

መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ።

Repent ye : for the kingdom of heaven is at hand.

ባርክ እግዚኦ ነገር ዘእምወንጌል ..... ረድኡ ወሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ሎቱ ስብሐት ወትረ እስከ ለዓለም ዓለም አሜን።

የሕያው እግዚአብሔር ልጅ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያውና ደቀ መዝሙሩ ከሚሆን ..... ወንጌል የተገኘው ቃል አባቱ ባርክ ምስጋና ዘወትር ገንዘቡ ነው ለዘለዓለሙ አሜን።

Bless, O Lord, the portion of the gospel of .... the disciple and apostle of our Lord Jesus Christ the Son of the living God ; to Him be glory continually, and unto the ages of ages. Amen.

የዕለቱ ወንጌል

Reading from the Gospel

ካህን/Priest

ይቀልል ሳልፈተ ሰማይ መምድር አምትደቅ

አሐቲ ቃል አምአሪት መአምነቢያት።

ከአሪትና ከነቢያት አንዲቱ ቃል ብትወድቅ

የሰማይና የምድር ማለፍ ይቀላል።

It is easier for heaven and earth to pass, than one tittle of the law to fall.

ማቴዎስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

ሕዝብ

ነአምን አበ ዘበአማን ወነአምን ወልደ ዘበአማን
ወነአምን መንፈስ ቅዱስ ዘበአማን ህልው
ሥላሴሆሙ ነአምን

አብን በእውነት አናምናለን ወልድንም በእውነት
እናምናለን መንፈስ ቅዱስንም በእውነት እናምናለን
የማይለወጥ ሦስትነታቸውን እናምናለን

We believe in the very Father, We believe in the very Son, and we believe in the very Holy Spirit, we believe in their unchangeable Trinity.

የሚርቆስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

ሕዝብ

እሱ ኪሩቤል ሙራፌል ያዐርጉ ሎቱ ስብሐት
እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ
እግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

እሊህ ኪሩቤልና ሱራፌል ምስጋናን ያቀርቡልታል
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ
አንተ እግዚአብሔር ነህ አያሉ።

Those cherubim and seraphim offer to Him glory saying; Holy Holy Holy art thou God, Father, Son and the Holy Spirit.

ሕዝብ/People

መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚኦ አንተ ውእቱ ዘትገብር መንክረ አርአይኮሙ ለሕዝብከ ኃይለከ ወአድነን ኮሙ ለሕዝብከ በመዝራዕትከ ፤ ሐርከ ውስተ ሲኦል ወአዕረገ ፄዋ እምህየ ወጸጎከነ ምዕረ ዳግመ ግዕዛነ እስመ መጻእከ ወአድነንከነ።

አቤቱ ከአማልክት ወገን የሚመስለህ ማነው? ተአምራትን የምታደርግ አንተ ነህ ለወገኖችህ ኃይልህን አሳየሃቸው ወገኖችህንም በክንድህ አዳንሃቸው ወደ ሲኦል ሄደህ ከዚያ ምርኮን አወጣህ ዳግመኛም አንድ ጊዜ ነጻነትን ሰጠኸን።

Who is like unto Thee, O Lord, among the gods? Thou art the God that does wonders, Thou has declared Thy strength among the people. With Thine arm Thou redeemed Thy people. Thou went into Hades and the captives rose up from there, and Thou did grant us again to be set free, for Thou came and saved us.

በእንተ ዝንቱ ንሴብሐከ ወንጸርሕ ኀቤከ እንዘ ንብል ቡሩክ አንተ እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ።

መጥተህ አድነኸናልና ስለዚህ እናመሰግንሃለን ፤ አቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቡሩክ ነህ እያልን እንጮኻለን መጥተህ አድነኸናልና።

For this cause we glorify Thee and cry unto Thee saying, Blessed art Thou, Lord Jesus Christ, for Thou did come and save us.

የዮሐንስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

ቀዳሚሁ ቃል ሙእቱ ቃል ቃለ እግዚአብሔር ሙእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐተ ፭ዱ ዋሕድ ከአቡሁ ቃለ አብ ሕያው ወቃል ሣሕየዊ ቃለ እግዚአብሔር ተንሥአ ወሥጋሁኒ ኢማሰነ።

ቃል በቅድሚያ ነበር ይህ ቃል እግዚአብሔር አብ ቃል ነው የቃል ሥጋ ሆነ ባሕርያችንን ተዋሐደ ካባቱ አንደአንድ ልጅ የሚሆን ክብሩንም አየን የሕያው የአብ ቃል ነው ያ ቃልም መድኃኒት ነው እግዚአብሔር ቃል ተነሣ ሥጋውንም መቃብር አላገኘውም።

In the beginning was the Word, the Word was the Word of God: The Word was made flesh, and dwelt among us, and we he held his glory, the glory as of the only-begotten of the Father, the Word of the living Father, and the life-giving Word, the Word of God, rose again and his flesh was not corrupted.

ዲያቆን

ፃኡ ንዑሰ ክርስቲያን

የክርስቲያን ታናሾች የሆናችሁ ውጡ

Go forth, Ye catechumens.

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ካህን

ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት

እግዚአብሔርን እንማልዳለን ፤ ሰው ወዳጅ

ሆይ ከቸርነትህ እንሻለን እንለምናለን።

Again we beseech the almighty God,

the Father of our Lord and Saviour,

Jesus Christ, we ask and entreat of

Thy goodness. O lover of man,

ካህን

አቤቱ ሐዋርያት የሰበሰቡዋትን አንዲት
የምትሆን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሰላም
አስብ ከዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ያለች

Remember Lord, the peace of the one holy apostolic Church which reaches from one end of the world to the other.

ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት ርትዕት በጎበ እግዚአብሔር።

ሐዋርያት ለሰበሰቡዋት በእግዚአብሔር ዘንድ ስለቀናች ፤ ክብርት ስለምትሆን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ጸልዩ።

Pray for the peace of the one holy apostolic church orthodox in the Lord.

ሕዝብ

ኪርያላይሶን

ኪርያላይሶን

Kyrie eleison.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት መማኅበርነ ውስቴታ

ክብርት ስለምትሆን ስለዚች ቤተ ክርስቲያን በውስጥዋ ስላለ አንድነታችንም ጸልዩ

Pray for this holy church and our congregation therein.

ሕዝብ

ማኅበረነ ባርክ ዕቀብ በሰላም

አንድነታችንን አጽንተህ በፍቅር ጠብቅ

Bless our congregation and keep them in peace.

ዲያቆን

ንበል ኩልነ በጥበበ እግዚአብሔር ጸሎተ ሃይማኖት

በእግዚአብሔር ጥበብ ሁነን ሁላችን የሃይማኖት ጸሎት እንበል

Let us all say, in the wisdom of God, the prayer of faith.

ጸሎተ ሃይማኖት

ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና
የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ
በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር....

The Prayer of Faith

We Believe in one God the Father almighty, maker of heaven, earth and all things visible and invisible.

ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም አናምናለን ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ ፤ በመለኮቱ ከአብ ጋራ የሚስተካከል።

And we believe in one Lord Jesus Christ, the only-begotten Son of the Father who was with Him before the creation of the world: Light from light, true God from true God, begotten not made, of one essence with the Father:

ሁሉ በእርሱ የሆነ ፤ ያለ እርሱ ምንም የሆነ የለም። በሰማይም በምድርም ያለ። ስለ እኛ ስለ ሰው ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ ፤ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም ሰው ሆነ።

By whom all things were made, and without Him was not anything in heaven or earth made: Who for us men and for our salivation came down from heaven, was made man and was incarnate from the Holy Spirit and from the holy Virgin Mary.

ሰው ሆኖ በጴንጤናዊ በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ። ታመመ፥ ሞተ ፥ ተቀበረም ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ። በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ።

Became man, was crucified for our sakes in the days of Pontius Pilate, suffred, died, was buried and rose from the dead on the third day as was written in the holy scriptures: Ascended in glory into heaven, sat at the right hand of His Father,

ዳግመኛ ሕያዋንን ሙታንንም ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም። ማሕየዊ በሚሆን ከአብ በሠረጸ በመን ፈስ ቅዱስም እናምናለን። እንሰግድለት ፤ እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋራ በነቢያት የተናገረ።

and will come again in glory to judge the living and the dead; there is no end of His reign. And we believe in the Holy Spirit, the life- giving God, who proceedeth from the Father; we worship and glorify Him with the Father and the Son; who spoke by the prophets;

ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት
በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን።
ኃጢአትን ለማስተሰረይ በአንዲት ጥምቀት
እናምናለን። የሙታንንም መነሣት ተስፋ
እናደርጋለን ፤ የሚመጣውንም ሕይወት ፤
ለዘለዓለሙ ፤ አሜን።

And we believe in one holy, universal, apostolic church; And we believe in one baptism for the remission of sins, and wait for the resurrection from the dead and the life to come, world with out end. Amen!

ሕዝብ (በዜማ)

ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ

ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም ፤ አሜን

የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን

የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ ፤ አሜን

And wait for the resurrection from the dead and the life to come, world with out end. Amen!

ካህን

እጄን ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ አንዳደረግሁ
እንደዚሁም ከሁላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ
ደፍራችሁ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ
ከርሱ ለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝምቾ

Also I am pure from the blood of you all. If you presumptuously draw nigh to the body and blood of Christ. As I have cleansed my hands from outward pollution, so I will not be responsible for your reception thereof.

ኃጢአታችሁ በራሳችሁ ይመለሳል እንጂ
በንጽህና ሆናችሁ ባትቀርቡ እኔ
ከበደላችሁ ንጹህ ነኝ።

I am pure of your wickedness, but
your sin will return upon your head if you do
not draw nigh in purity.

<u>ዲያቆን</u>

ይህን የካህኑን ቃል ያቃለለ ወይም የሳቀና የተነጋገረ

If there be any who disdains this word of the priest or

ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክፉት የቆመ ቢኖር ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳሳዘነው በርሱም እንደተነሣሣ ይወቅ ይረዳ ፤ ስለ በረከት ፈንታ መርገምን ፤ ስለ ኃጢአት ሥርየት ፈንታም ገሃነመ እሳትን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላል።

laughs or speaks or stands in the church in an evil manner, let him know and understand that he is provoking to wrath our Lord Jesus Christ, and bringing upon himself a curse instead of a blessing, and will get from God the fire of hell instead of the remission of sin.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሡ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለን

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስክ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ካህን:- ጸሎተ አምኃ (የሰጦታ ጸሎት)

ለዘለዓለሙ ገናና የምትሆን እግዚአብሔር ሆይ! ያለጥፋት ሰውን የፈጠርኸው። አስቀድሞ በሰይጣን ቅንዓት የገባውን ሞት ሕያው በሚሆን ልጅህ በጌታችን በአምላካችንና መድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት አጠፋህ።

“Prayer of Salutation” of St. Basil :

God, great eternal, Who did form man incorrupt, Thou did abolish death that came first through the envy of Satan, by the advent of Thy living Son our Lord, God, and Saviour Jesus Christ,

የሰማይ ሠራዊት እንዲህ እያሉ አንተን ያመሰግኑባትን ከሰማይ የተገኘች ሰላምን በምድር ሁሉ መላህ በሰማይ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይገባል ፤ ምድርም ሰላም የሰው ፈቃድ

and Thou did fill all the earth with Thy peace which is from heaven wherein the armies of heaven glorify Thee saying : Glory to God in heaven and on earth peace, His goodwill toward men.

ሕዝብ

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት
ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ

በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል
በምድርም ሰላም ፤ የሰው ፈቃድ

Glory to God in heaven and on earth peace, His goodwill toward men.

ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ ሰላም ፍጽምት መፍቅር
ተአምቱ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት

ፍጽምት ሰለምትሆን ሰላምና ፍቅር
ጸልዩ ፤ እርስ በርሳችሁ በተለየች እማኄ
እጅ ተነሳሱ።

Pray for the perfect peace and love. Salute one another with a holy salutation.

ሕዝብ

ክርስቶስ አምላክነ ረስየነ ድልዋነ ከመን ትአማኅ በበይናቲነ በአምኃ ቅድሳት።

አምላካችን ክርስቶስ ሆይ እርስ በርሳችን በተለየች እማኔ እጅ እንነሳሳ ዘንድ የበቃን አድርገን።

Christ our God, make us meet to salute one another with a holy salutation.

ካህን/Priest

ወንትመጦ እንበለ ኩነኔ እምሀብትከ ቅድስት እንተ ይእቲ እን በለ ሞት ሰማያዊት በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈከ ስብሐት ወእሊዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ክብርት ከምትሆን ሰጦታህ ሳይፈረድብን እንቀበል፤ ይህችውም የማታልፍ ሰማያዊት ናት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ከርሱ ጋር ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ለአንተ ይገባል ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

And to partake, without condemnation, of Thy holy immortal heavenly gift, through Jesus Christ our Lord : Through whom to Thee with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and unto the ages of ages. Amen.

ምሉ፡ቅር ወፊዱ።
ወላዲቱ፡ አምላክ

ካህን/Priest

አኮቴተ ቊርባን ዘእግዝተነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዘደረሰ በመንፈስ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስለ ምስለ ኩልነ ሕዝበ ክርስቲያን ወይዕቀባ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

የብሕንሳ ኤጲስ ቆጶስ አባ ሕርያቆስ አምላክን ስለ ወለደች ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ የደረሰው የቊርባን ምስጋና ይህ ነው። ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋራ ይኑር ለዘላለሙ አሜን።

The Anaphora of our Lady, the Virgin Mary, mother of God, which Abba Heryacos, Bishop of the province of Behensa composed through the Holy Spirit. May his prayer and blessing be with our ….. world without end. Amen.

ካህን

እግዚአብሔር ምስለ ኩልክሙ

እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋራ ይሁን

The Lord be with you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋራ

And with Thy spirit.

ካህን

አእኩትዎ ለአምላክነ

አምላካችንን አመስግኑት

Give ye thanks unto our God.

ሕዝብ

ርቱዕ ይደሉ

እውነት ነው ይገባል

It is right, it is just.

ካህን

አልዕሉ አልባቢክሙ

ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ

Lift up your hearts.

ሕዝብ

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ

በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን

We have lifted them up unto the Lord our God.

ካህን/Priest

ልቡናዬ በጎ ነገርን አወጣ። ልቡናዬ በጎ ነገርን አወጣ። ልቡናዬ በጎ ነገርን አወጣ። እኔም የማርያምን ቅዳሴ እናገራለሁ፤ በማብዛት አይደለም በማሳነስ ነው እንጂ

My heart exclaims a good deliberation ; my heart pours forth a worthy concept ; my heart gushes a noble oracle.

እኔም የድንግልን ውዳሴ እናገራለሁ።
መዘንጋት ባለበት ቃል በማሰረዘም
አይደለም በማሳጠር ነው እንጂ። እኔም
የድንግልን ገናንትዋን እናገራለሁ።

And I speak of the Anaphora of Mary, not at length but briefly. And I speak the praise of the Virgin, not in many words, which would be forgotten, but in few. And I speak of the exaltation of the Virgin.

ዛሬ በዚህች ቀን በፍቅርና በትሕትና ግሩም በመሚሆን በዚህ ምሥጢር ፊት አቆማለሁ። በዚህም ማዕድና ቍርባን ፊት።

And today I stand, this very day, in humility and love before this mighty mystery and before this table and offering.

መንፈሳቸውን ያረከሱ ሰዎች ከርሱ ሊቀምሱ የማይቻላቸው በእውነት ቍርባን ነው። በበግ በጊደርና በላም ደም እንደነበረው እንደ ቀደሙት አባቶች መሥዋዕት አይደለም፤ እሳት ነው እንጂ።

Truly this is the offering which those whose spirits are defiled cannot taste. It is not like the sacrifice of the forefathers which depended upon the blood of sheep, oxen and cows, but it is fire.

ፈቃዱን ለሚሠሩ ልቡናቸውን ላቀኑ ሰዎች የሚያድን እሳት ነው። ስሙን ለሚክዱ ለዓመፀኞች ሰዎች የሚባለ እሳት ነው።

እሳታውያን የሚሆኑ ሱራፌልና ኪሩቤል ሊነኩት የማይቻላቸው በእውነት እሳት ነው።

It is fire, giving life to the upright in heart who fulfill His will. It is a consuming fire to the unrigh-teous who deny His name. Truly it is a fire that even the fire clad cherubim and seraphim cannot touch.

ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን፤ ከፍ ከፍም እናደርግሻለን እውነተኛ የጽድቅ መብልንና እውነተኛ የሕይወት መጠጥን ወልደሽልናልና። የሐዋርያት ተከታዮች የሆናች ሁ በአንብሮ እድ የተሾማች ሁ አባቶች ሆይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእኛ የምታማልዱ እናንተን ተቀብለናች ኋል

O Mary, for this we love and exalt you, because you bore for us the true Food of righteousness and the true Drink of life. O our fathers, consecrated by the laying on of hands, successors of the apostles, whom we have taken as intercessors towards God,

www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእኛ የሚያማልዱ እነዚህንም ሁለቱን የጳጳሳት አለቆች በዘመናችን ተቀብለናቸዋል። የታላቂቱን አገር የኢትዮጵያን ..... በአባቶቻችንም አገር ከተማ ላይ ክቡር የሚሆን አባ .....

also, during our days, we take as representatives between us and God these two: The Patriarch of the great City of (_____), Abba (_____), and the blessed Arch-bishop, Abba (_____), the primate of our country.

ዲያቆን/Deacon

በእንተ ብፅዕት ወፍስሕት መስብሕት በኩሉ ፤ ወቡርክት ወቅድስት ወንጽሕት ፤ እግዝእትነ ወለዲተ አምላክ ማርያም ድንግል።

ብፅዕትና ፍስሕት በሁሉ ዘንድ የተመሰገነች ፤ ቡርክትና ቅድስት ንጽሕትም ሰለሆነች ሰለ አምላክ እናት ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም

For the sake of the blessed, happy, prosperous, holy and pure Virgin Mary, our Lady, Parent of God, glorified by all.

www.ethiopianorthodox.org

ንፍቅ ካህን/*Assistant priest*

ልዩ ሦስት አቤቱ ዓለሙን ሁሉ የያዝህ ፤ በቃልህ ሥልጣን ደገኛና ድንቅ ሥራን የሠራህ።
ምሥራቁንና ምዕራቡንs ፤ ሰሜኑንና ደቡቡን ፣ መስዑንና አዜቡን ባርክ ሰማይና ምድርን ባሕሩንና ወንዞቹን የውኃውንም ፈሳሾች የውኃውንም ምንጭ ሁሉ ባርክ።

O holy Trinity, Who holds the whole world, who has done great and wonderful deeds through the power of Thy word, bless the east and the west, the north and the south, the north east and the south east, (the north west and the south west), bless the heaven, the earth, the sea, the rivers, the source of water, and all the springs of water.

ንፍቅ ካህን/*Assistant priest*

ልዩ ሥሰት የምትሆን አብ ወልድ መንፈስ
ቅዱስ ሆይ የሚፋቀሩ የክርስቶስ ወገኖች
የሚሆኑ ሕዝብህን በሰማያውያንና
ምድራውያን በረከት ባርክ።

O Holy Trinity, Father, Son, and Holy Spirit, bless Thy people, beloved Christians, with heavenly and earthly blessings.

በእኛም ላይም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋን ላክ ፤
የቅድስት ቤተ ክርስቲያንህንም ደጅች በምህረትና
በሃይማኖት እንዲከፈቱ አድርግልን ፤
እስከ መጨረሻይቱ ሐቅታም ድረስ ልዩ ሦስትነትህን
ማመንን ፈጽምልን።

And send upon us the grace of the Holy Spirit, and keep the doors of Thy holy church open unto us in mercy and in faith; and perfect unto us the faith of Thy holy Trinity unto our last breath.

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የታመሙ ወገኖችህን ጎብኝ ፤ የሄዱትንና እንግዶች የሆኑትን አባቶቻችንን ወንድሞቻችንን መርተህ በሰላምና በጤና ወደ ቤታቸው መልሳቸው።

O my Lord Jesus Christ, visit the sick of Thy people ; heal them ; and guide our fathers and our brethren who have journeyed, becoming strangers : bring them back to their dwelling places in peace and in health.

የሰማዩን ነፋስ ባርክ ዝናሙንም በዚህች ዓመት
የሚያፈራውን የምድሩን ፍሬ እንደ ቸርነትህ ባርክ ፤
ዘወትር ተድላንና ደስታ አድርግ ፤ ሰላምህንም
አጽናልን ፤ ሁልጊዜ ለኛ በጎ ነገርን ሊያደርጉልን
ጽኑዓን የሚሆኑ የታያላኑን ልቡና መልስ።

Bless the airs of heaven, and the rains and the fruits of the earth of this year, in accordance with Thy grace, and make joy and gladness prevail perpetually on the face of the earth.

በቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ሁልጊዜ ለሚሰበሰቡ ለቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ፍቅርን ስጥ ፤ ለሁሉም ለያንዳንዱ በየስማቸው ኃያላን በሚሆኑ ፊት ሰላምን አብዛላቸው ፤ አምላካችን ሆይ በቀናች ሃይማኖት ሆነው ያንቀላፉትንና ያረፉትን ያባቶቻችንንና የወንድሞቻችንን የእኅቶቻችንን ም ነፍስ አሳርፍ።

And confirm for us Thy peace. Turn the hearts of mighty kings to deal kindly with us always. Grant peace to the scholars of the church who are continually gathered in Thy holy church; Rest the souls of our ancestors, both our brothers and sisters who have fallen asleep and gained their rest in the right faith.

አምላካችን ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ዋጋቸውን ይከፍላቸው ዘንድ እጣንና ቍርባን ወይንና ሜሮን ዘይትም መጋረጃም የንባብ መጻሕፍቶችን የቤተ መቅደስንም ንዋያት በመስጠት የሚያገለግሉትንም ባርክ።

And bless those who give gifts of incense, bread and wine, ointment and oil, hangings and reading books, and vessels for the sanctuary, that Christ our God may give them their reward in the heavenly Jerusalem.

ይቅርታን ያገኙ ዘንድ ከእኛ ጋራ የተሰበሰቡትንም ሁሉ አምላካችን ክርስቶስ ሆይ ይቅር በላቸው ፤ በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ በመንበርህ ፊት ምፅዋት ያመጡትንም ሁሉ ተቀበላቸው። የተጨነቀችይቱንም ነፍስ ሁሉ አሳርፍ። በሰንሰለት የታሰሩትን በስደትና በምርኮ ያሉትንም።

And all of them that are assem-bled with us to entreat for mercy, Christ our God have mercy upon them : and all them that give alms before Thine awful and terrifying throne, receive. And comfort every straitened soul, them who are in chains and them who are in exile or captivity.

መሪር በሆነ አገዛዝ የተያዙትንም አምላካችን ሆይ በቸርነትህ አድናቸዉ ፤ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ወደአንተ በምንማልድት ጊዜ እን ድናስባቸዉ ያዘዙንም ሁሉ በሰማያዊት መንግሥትህ አስባቸዉ።

And them that are held in bitter servitude, our God, deliver them in Thy mercy. And all of them that have entrusted it to us to remember them in our supplications to Thee O our Master Jesus Christ, remember them in Thy heavenly kingdom.

ኃጥዕ ባርያህን አኔንም አስበኝ ፤ አቤቱ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ ፤ ጠብቃቸዉ አስከ ዘለዓለምም ድረስ ከፍ ከፍ አድርጋቸው።

And remember me, thy sinful servant. O Lord, save thy people and bless Thine inheritance *(+ over the people),* feed them and lift them up for ever.

ዲያቆን/Asst. Deacon

መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ለሊቃን ጳጳሳት፤ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኩሉሙ ሕዝበ ክርስቲያን።

አቤቱ የጳጳሳቱን አለቃ ጳጳሳቱን፤ ኤጲስ ቆጶሳቱን፤ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱ፥ የክርስቲያን ወገኖችን ሁሉ ማራቸው፤ ይቅርም በላቸው።

Lord pity and have mercy upon the patriarchs, archbishops, bishops, priest, deacons and all the Christian people.

ካህን/Priest

አማላጅቱ ሆይ! እሊሀንም ሁሉንም ከልጅሽ ዘንድ አማልጂ፤ የጳጳሳትንና የሊቃነ ጳጳሳትን የኤጲስ ቆጳሳትንም ሁሉ ነፍስ ያሳርፍ ዘንድ የቀሳውስትንና የዲያቆናትንም፤ እውነተኛውን የቃል ጎዳና የሚያቀኑ።

O Intercessor, intercede with your Son for the sake of each and all, to give rest to the souls of all the patriarchs, archbishops, bishops, priests and deacons who keep straight the way of the true word:

ነገሥታቱንና መኳንንቱን መሳፍንቱንም በሥልጣን
የሚኖሩትን ወይዛዝርቱንና ደናግልን፤ መነኰሳትንም
ባለፀጋውንና ድሀውን፤ ታላቁንና ታናሹንባልቴቲቱንና
አባት እናት የሞቱበትን፤ መጻተኛውንና ችግረኛውን።
አስቀድሞ ከቤተ ክርስቲያን ማኅበር ተለይተው
ያረፉትን የክርስቲያንንም ወገኖች ሁሉ።

kings, rulers, princes, those in authority,
young men, virgins, monks, rich, poor, great,
small, old women, orphans, sojourners,
miser-able, and all Christian people from the
congregation of the church who in days
gone by have gone to their rest.

ይልቁንም በዚህች ቦታ ስለሞቱ አንቺ ስለእነርሱ ተግተሽ አማልጂ፤ ነፍሳቸውን ዕረፊፍትን ሰጥቶ ያሳርፍ ዘን ድ።የድል ነሺዎች የሰማዕታት ቦታ በተባለ ሁሉ ዘንድ፤ በቡሩካን ጻድቃን ቦታና በትጉሃን መላእክት ቦታ። በቦታው ሁሉ ዘንድ አንቺ ርስት ነሽ፤ ስምሽም በእግዚአብሔር ዘንድ የሠለጠነ ነው።

Make earnest intercession for those who have fallen asleep in this place that He (Thy Son) may give their souls a quiet rest, in every place which is called the place of the victorious martyrs, in the place of the blessed righteous, in the place of the watchful angels. You are the inheritance in every place, and your name is acceptable before God.

www.ethiopianorthodox.org

ዲያቆን/Deacon

እለ ትነብሩ ተንሥኡ

የተቀመጣችሁ ተነሡ

Ye that are sitting, stand up.

ካህን/Priest

እግዚአብሔርን በመፍራት እንነሣ ምስጋናንየተመካች እርስዋን ከፍ ከፍ እናደርጋት ዘንድ እንዲህም እያልን እናመሰግናት ዘንድ ጸጋን የተመላሽ ሆይ! የደስታ መፍሰሻ ሆይ! ዓይኖቻቸው ብዙዎች ከሚሆኑ ከኪሩቤል ክንፎቻቸው ስድስት ከሚሆኑ ከሱራፌልም ይልቅ የሚበልጥ የመልክ ግርማ አለሽ።

Let us stand up in the fear of God to exalt and glorify her who is full of glory saying, O you who are full of grace, O you who are the channel of joy, you have a countenance more beautiful than the many-eyed che-rubim and the six-winged seraphim.

ዲያቆን/Deacon

ውስተ ጽባሕ ነጽሩ

ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ

Look to the east.

ካህን/Priest

እግዚአብሔር አብ በሰማይና ሁኖ ምሥራቅንና ምዕራብን፤ ሰሜንንና ደቡብን ዳርቻዎችንም ሁሉ በእውነት ተመለከተ። ተነፈሰ አሸተተም እንደ አንቺ ያለ አላገኘም፤ የአንቺን መዓዛ ወደደ፤ ደም ግባትሽንም ወደደ። የሚወደውን ልጁንም መዳንቺ ሰደደ።

Truly God the Father looked down from heaven towards the east, the west, the north and the south, and towards all the ends (of the earth). He breathed in every savour (3), and found none like unto you. He approved your savour and loved your beauty and so sent to you His beloved Son.

ዲያቆን/Deacon

እናስተውል።

Let us give heed.

ካህን/Priest

አንቺን የወደደ እግዚአብሔር አብ ቅዱስ ነው፤ በማኅፀንሽ ያደረ ወልድ ዋሕድም ቅዱስ ነው፤ ያጸናሽ የጽድቅ መንፈስ ጸራቅሊጦስም ቅዱስ ነው።

Holy is God the Father Who loved you, holy is the only-begotten Son Who abode in your womb, and holy is the Paraclete, the Spirit of righteousness, Who strengthened you.

ዲያቆን/*Deacon*

አውሥኡ

ተሰጥዎን መልሱ

Answer ye.

ሕዝብ/*People*

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምሥጋና በሰማይና በምድር የመላ ነው።

Holy, holy, holy, perfect Lord of hosts, heaven and earth are full of the holiness of Thy glory.

ካህን/Priest

ምስጋናን የተመላሽ ድንግል ሆይ በማንና በማንስ ምሳሌ እን መስልሻለን። አማኑኤል የማይተረጎም የሥጋን ልብስነት ከአን ቺ የለበሳት መሥሪያ ነሽ። ዝሐዉን ከአዳም ጥንተ ሥጋ አደረገ። ማጉም ያንቺ ሥጋ ነዉ ፤ መወርወሪያዉም ቃል እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ።

O Virgin, full of glory, with whom or with what likeness shall we liken you? You are the loom from which Emmanuel took his ineffable garment of flesh. He made the warp from the same flesh as that of Adam, and the woof is your flesh. The shuttle is the Word himself, Jesus Christ.

መሕኑም ከልዕልና የወረደ የልዑል እግዚአብሔር አምሳል ነዉ። ሠሪዉም መንፈስ ቅዱስ ነዉ። ወዮ ይህ ነገር ዕጹብ ድንቅ ነዉ የቀደሙ አባቶች ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገሩብሽ ድልድይ ሆይ ከምድር እስከ ሰማይ የምትደርሽ መሰላል ሆይ የፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ በአንቺ ታደሰ።

The length of the warp is the shadow of God the Most High. the weaver is the Holy Spirit. How marvellous and wonder-ful is this thing ! O bridge over which the ancient fathers crossed from death unto life! O ladder from earth to heaven, through you the first creation was renewed.

www.ethiopianorthodox.org

ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ። በግፍ የተገደለ የአቤል የውሃቱ አንቺ ነሽ። የሴት ቸርነት አንቺ ነሽ።የሄኖክም ሥራዎቹ ከክፉ ጥፋት የዳነባት የኖኅ መርከብ የሴም ቡራኬው ዕድል ፈንታውም አንቺ ነሽ።

You were the hope of Adam when he was driven out from paradise, the meekness of Abel who was killed through unrighteousness, the kindness of Seth, the works of Enoch, the ark of Noah through which he was saved from evil's destruction, the blessing and portion of Shem,

የአብርሃም እንግድነት የይስሐቅ መዓዛ፤ የያዕቆብም መሰላልአንቺ ነሽ። የዮሴፍንም የምታረጋጊው እንቺ ነሽ። የሙሴ ጽላት ጸጦስ የተባለች የሲና ዕፅ፤ በካህን አሮን ልብስየነበረች ጸናጽል፤ ዳግመኛም የበቀለችና ያበበች ያፈራችም በትር አንቺ ነሽ።

the tent of Abraham, Isaac's savour, the ladder of Jacob, Joseph's comforter, the tables of Moses, the bush at Sinai, the bells on the garment of Aaron the priest, his rod which sprouted, blossomed and bore fruit,

የኢያሱ የምስክሩ ሐውልት የጌዴዎን ፀምር የሳሙኤል የሸቱሙዳይና የዘይት ቀንድ አንቺ ነሽ። የተመከበት የእሴይ ሥር፤የአሚናዳብም ሠረገላ የደዊት መሰንቆ የሰሎሞንም አክሊል አንቺ ነሽ። የታጠረች ተክል የተዘጋች የውኃ ጕድጓድ አንቺ ነሽ።

Joshua's stone of testimony, the fleece of Gideon, Samuel's jar of ointment and horn of oil, Jesse's root of which he boasted, the chariots of Amminadib, David's harp, the crown of Solomon, the enclosed garden, the sealed spring,

የኤልያስ የወርቅ መሶብ፤ የኤልሳዕ ጋን አንቺ ነሽ። ኢሳይያስ ፅንሰን ከድንግልና ጋራ የተናገረ ልሽ ዳንኤልም ያለ ሩካቤ መውለድን የተናገረ ልሽ አንቺ ነሽ።

Elijah’s golden measure, Elisha’s cruse, the conceiving virgin whom Isaiah prophesied, the first to give birth without intercourse of which Daniel (also spoke).

ፋራን የምትባል የዕንባቆም ተራራ፤ የተዘጋች የሕዝ
ቅኤል ምሥራቅ፤ የቤተ ልሔም ሕግ መውጫ ኤፍ
ራታ የምትባል ምድር አንቺ ነሽ። የሲሎንዲስ ዕፀ
ሕይወት የናሆምንም ቁስል የምታድን የዘካርያስ ደስ
ታው፤ የሚልክያስ ንፅሕት አዳራሽ አንቺ ነሽ።

Habakkuk’s mountain of Pharan, Ezekiel’s closed house in the east, Micah’s place in Bethlehem from which the law goes forth, the land of Ephratah, Silondis’ tree of life, the healer of Nahum’s wounds, Zechariah’s rejoicing, the clean hall of Malachi.

ድንግል ሆይ የነቢያት ትንቢትና ምሳሌ የሐዋርያት ሞገሳቸው፤የሰማዕታት እናታቸው፤ የመላእክትም እሳታቸው አንቺ ነሽ። በመዓልትና በሌሊት በበሮችዋ ደጅ የሚጠኑ የወራዙትና የደናግል የመነኰሳትም መመኪያቸው አንቺ ነሽ።

O Virgin, you are the ideal and the prophecy of the prophets, the favour of the apostles, the mother of martyrs ; the sister of angels ; the boast of the young men and virgins and the monks who are watchful day and night at your gates.

ድንግል ሆይ በኃጢአት ፍትወት የተፀነስሽ
አይደለም፤ በሕግ በሆነ ሩካቤ ከሐና ከኢያቄም
ተወለድሽ እንጂ።

O Virgin, you were not conceived through unclean lust, but in lawful marriage you were born from Hannah and Joachim.

ድንግል ሆይ አንገታቸውን እንደሚያገዝፉ እንደ
ዕብራውያን ሴቶች ልጆች በዋዛ ያደግሽ አይደለም፤
በንጽሕና፤ በቅድስና በቤተ መቅደስ ኖርሽ እንጂ።

O Virgin, you were not conceived through unclean lust, but in lawful marriage you were born from Hannah and Joachim.

ድንግል ሆይ ምድራዊ ኅብስትን የተመገብሽ
አይደለሽም ከሰማየ ሰማያት የበሰለ ሰማያዊ ኅብስትንነ
ው እንጂ። ድንግል ሆይ ምድራዊ መጠጥን የጠጣሽ
አይደለም፤ ከሰማየ ሰማያት የተቀዳ ሰማያዊ መጠጥን
ነው እንጂ።

O Virgin, you did not eat earthly bread but heavenly bread prepared in the heaven of heavens. O Virgin, you did not drink earthly drink, but heavenly drink poured from the heaven of heavens.

ድንግል ሆይ ከአንቺ አስቀድሞ ከአንቺም በኋላ
እንዳሉ ሴቶች እድፍ የምታውቂ አይደለሽም
በንጽሕና፤ በቅድስና ያጌጥሽ ነሽ እንጂ።

O Virgin, you did not know uncleanness like the women who were before you, and would come after you, but you are adorned with holiness and purity.

ድንግል ሆይ የሚያታልሉ ጒልማሶች ያረጋጉሽ አይደለሽም የሰማይ መላእክት ጐበኙሽ እንጂ። እንደ ተነገረ ካህናትና የካህናት አለቆች አመሰገኑሽ እንጂ።

O Virgin, the depraved young men could not entice you, but the angels of heaven visited you, and, as it was said, the priests and the high priests praised you.

ድንግል ሆይ ለዮሴፍ የታጨሽ ለመገናኘህ
አይደለም፤ንጹሕ ሆኖ ሊጠብቅሽ ነው እንጂ።
እንዲሁ ሰለ ሆነ።

O Virgin, you were not espoused to Joseph for coming together, but in order that he might keep you in purity, and thus it was fulfilled.

እርሱ ቅሉ እግዚአብሔር አብ ንጽሕናሽን ባየ ጊዜ ስሙ ገብርኤል የሚባል ብርሃናዊ መልአኩን ወደ አንቺ ላከ መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ይመጣል የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል አለሽ።

When God the Father saw your purity He sent you his radiant angel, named Gabriel, and he told you: “The Holy Spirit shall come upon you, and the power of the Highest shall overshadow you.”

ከአባቱ አጠገብ ሳይለይ፤ ቃል ወደ አንቺ መጣ፤
ሳይወሰን ፀነስሽው በላይ ሳይጐድል በታች
ሳይጨመር በማኅፀንሽ ተወሰነ።

The Word came to you without being separated from the bosom of His Father; you conceived Him without His being limited, and He stayed in your womb without making subtraction from above or addition beneath.

መመጠንና መመርመር የሌለበት እሳተ መለኮት በሆድሽ አደረ። በምድራዊ እሳት እንመስለው ዘንድ አይገባም ለእሳትስ መጠን አለው፤ ልክም አ ለው፤ መለኮት ግን ይህን ያህላል፤ ይህንንም ይመስላል ሊባል አይቻልም።

There abode in your womb the inestimable and immeasurable fire of the godhead. It is not just to compare Him with earthly fire. Fire has limits and volume, but of the Deity, it cannot be said that it is like this or even seems to be like this.

ለመለኮት እንደ ፀሐይና እንደ ጨረቃ ክበብ፤ እንደ ሰውም መጠን ያለው አይደለም፤ ድንቅ ነው እንጂ፤ የሰው ሕሊና የመላእክትም አእምሮ በማይደርስበት በአርያሙ የሚኖር ነው እንጂ።

The Godhead has no circuit like the sun and moon, nor stature like man, but He is mighty and sitting in His highest heaven which neither the thought of man nor the knowledge of angels can reach.

ለመለኮት ወርድና ቁመት፤ ላይና ታች፤ ቀኝና
ግራ ያለው አይደለም፤ በሁሉ የመላ ነው እንጂ።

The Godhead has no circuit like the sun and moon, nor stature like man, but He is mighty and sitting in His highest heaven which neither the thought of man nor the knowledge of angels can reach.

ለመለኮት የሚዘረጋንትና የሚሰበስብበት ያለው አይደለ ም፤ ግዛቱበሀገሩ ሁሉ ነው እንጂ። ለመለኮት በላይ ጠፈር በታችም መሠረት ያለው አይደለም፤ ጠፈሩ እር ሱ መሠረቱም እርሱ ነው እንጂ።

The Deity has no place wherein to stretch or contract himself but He fills every place. The Deity has neither firmament above nor foundation beneath, but He is Himself the firmament and the foundation.

ለመለኮት ከምድር ከውስጥዋ የሆነውን ያነሳ ዘንድ
ማጐንበስ ራስንም ዝግ ማድረግ ያለበት አይደለም፤
ለጴጥሮስ እንዳሳየው ሁሉ በእጁ የተያዘ ነው እንጂ
።

The Deity does not stoop nor bow down the head to take up that, which is on earth, but al is in His hand as He showed Peter.

ለመለኮት በሚታይ ገንዘብ በሚወሰንም ገንዘብ ደረትና ፊት የኋላም ጀርባ ያለው አይደለም፤ በነደ እሳት የተሸፈነ ነው እንጂ። ነደ እሳት ግን እርሱ ነው። መለኮትስ ንጹሕና ፅሩይ ብሩህም ነው።

The Deity has neither chest nor back by which he can be seen, and through which He can be limited, but He is covered with the flame of fire and He is Himself the flame of fire. The Deity is clean, pure, and bright.

የላከ አብን በሕላዌው አባት እንደሆነ እናምናለን። የተላከ ወልድንም በሕላዌው ወልድ እንደሆነ እናምናለን። ማሕየዊ መንፈስቅዱስንም በሕላዌው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እናምናለን። ሦስቱሰም አንዱ እግዚአብሔር።

We believe that the Father Who sends is Father in His nature. We believe that the Son Who is sent is Son in His nature. We believe that the life-giving Holy Spirit is Holy Spirit in His nature. Three names but one God.

አብርሃም ከይስሐቅ እንደሚበልጥ፤ ይስሐቅም ከያዕቆብ እንደሚበልጥ አይደለም። ለመለኮት እንዲህ አይደለም፤ አብ ከልጁአይበልጥም። ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም። መንፈስ ቅዱስም ከወልድ አያንስም። ወልድም ከአባቱ አያንስም።

It is not with the Deity as it was with Abraham who was older than Isaac, or with Isaac who was older than Jacob, but the Father is not older than the Son, neither is the Son older than the Holy Spirit, and the Holy Spirit is not younger than the Son, neither is the Son younger than His Father.

አብርሃም በፍጥረት ሥርዓት ይስሐቅን እንደሚያዘው ይስሐቅምያዕቆብን እንደሚያዘው አይደለም። መለኮት እንዲህ አይደለም፤አባት በመሆን አብ ልጁን አያዝዘውም። ወልድም ልጅ በመሆንአይበልጥም፤ መንፈስ ቅዱስም ትክክል ነው።

It is not with the Deity as it was with Abraham who gave commands to Isaac, or with Isaac who gave orders to Jacob, but the Father, being Father, does not give orders to the Son ; and the Son, being Son, is not exalted; and the Holy Spirit.

መለኮት ግን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው። አንድ አምላክ አንዲት መንግሥት፤ አንዲት ስልጣን፤ አንዲት አገዛዝ ናቸው።

But the Divine Father, Son and Holy Spirit are one God, one kingdom, one authority and one government.

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያስባሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይናገራሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይወዳሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይመክራሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይናገራሉ።

The Father, the Son and the Holy Spirit think.
The Father, the Son and the Holy Spirit speak.
The Father, the Son and the Holy Spirit approve.
The Father, the Son and the Holy Spirit take counsel.
The Father, the Son and the Holy Spirit utter the word.

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይፈጽማሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይሠራሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያስማማሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያከናውናሉ።

The Father, the Son and the Holy Spirit complete.
The Father, the Son and the Holy Spirit create.
The Father, the Son and the Holy Spirit unite.
The Father, the Son and the Holy, Spirit create well.

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይልካሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያሠለጥናሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ምስክር ይሆናሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሰውን ይስባሉ።

The Father, the Son and the Holy Spirit send.
The Father, the Son and the Holy Spirit give authority.
The Father, the Son and the Holy Spirit hear witness.
The Father, the Son, and the Holy Spirit draw.

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያለምዳሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይመክራሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያነጻሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያጸራሉ።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያከብራሉ።

The Father, the Son, and the Holy Spirit accustom.
The Father, the Son, and the Holy Spirit advise
The Father, the Son, and the Holy Spirit purify.
The Father, the Son, and the Holy Spirit cleanse.
The Father, the Son, and the Holy Spirit hallow.

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያጸናሉ።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያስጨክናሉ።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያስተምራሉ።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይጋርዳሉ።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያለብሳሉ።

The Father, the Son, and the Holy Spirit strengthen.
The Father, the Son, and the Holy Spirit encourage.
he Father, the Son, and the Holy Spirit teach.
The Father, the Son, and the Holy Spirit crown.
The Father, the Son and the Holy Spirit clothe.

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ባለሟል ያደርጋሉ።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይቀጣጣሉ።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይፈርዳሉ።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይመረምራሉ።

The Father, the Son, and the Holy Spirit grant grace.
The Father, the Son, and the Holy Spirit sit.
The Father, the Son, and the Holy Spirit judge.
The Father, the Son, and the Holy Spirit examine.

እንዲሀ እናምናለን እንዲሀም እንታመናለን አንድነትን ሳን ለይ የተለየ እንዳይሆን። የተቀላቀለ እናዳይሆን እንለይ። እንደ አብርሃምና እንደ ይስሐቅ ያዕቆብም ሦስት የምንል አይደለንም በገጽ ሦስት ሲሆን አንድ ነው እንጂ። ከፍጥረት ሁሉ እንደሚቀድም እንደ አዳም አንድ የምንል አይደለም በባህርይ አንድ ሲሆን ሦስት እንላለን አንጂ።

Thus we, without separating or dividing, believe and confess the oneness and unity so that it will not be divided or separated. Let us distinguish so that it will not be confused. We do not say “three” as we say Abraham, Isaac and Jacob, but one is three persons. We do not say One like Adam the first creature, but three with one nature.

ክፎች አይሁዳን፤ ባለማወቃቸው የእግዚአብሔር ገጽና አካል አንድ ነው የሚሉ በደለኞቹን የይስማኤል ወገኖችንም እነሆ እንሰማቸዋለን፤ ልቡናቸውን ያሳወሩ ነቸው። አምላካቸው ብዙ አጋንንቶቻቸውም ብዙ የሆኑ በጣዖት የሚያመልኩ አረማዊያንን እነሆ እናያቸዋለን።

Now we hear the wicked Jews and the unrighteous Ishmaelites, who, being without understanding, say God is one person and one body ; they are of a blind heart. Now we see the idolatrous heathen whose idols are many and whose devils are many.

እኛ ግን በጎ ጎዳና የሚያስተምሩትን እንከተላለን ሐዋርያት እንዲህ እያሉ እንዳስተማሩን።
አብ ፀሐይ ነው፤ ወልድ ፀሐይ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ፀሐይ ነው፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን አንድ የእውነት ፀሐይ ነው።

But we follow the leaders to the good way as the Apostles taught us saying : it is as if The Father is the sun, the Son is the sun, and the Holy Spirit is the sun : but it is one sun of righteousness over all.

አብ እሳት ነው፤ ወልድ እሰት ነው፤ መንፈስ ቅዱስም እሳት ነው፤ በልዕልና ያለ አንድ የሕይወት እሳት ነው። አብ ጎሕ ነው፤ ወልድ ጎሕ ነው፤ መን ፈስ ቅዱስም ጎሕ ነው፤ በብርሃኑ ፀዳለ ጨለማ የራቀበት አንድ የጧት ጎሕ ነው።

The Father is fire, the Son is fire, and the Holy Spirit is fire ; but it is one fire of life in the highest heaven. The Father is the dawn, the Son is the dawn, and the Holy Spirit is the dawn : but it is a single eastern dawn through which, by the ray of its light, the darkness was destroyed.

አብ ጕንደ ወይን ነው፤ ወልድ ጕንደ ወይን ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ጕንደ ወይን ነው፤ ዓለሙ ሁሉ የጣፈጠበት አንድ የሕይወት ወይን ነው። አብ ሐሊብ ነው፤ ወልድ ሐሊብ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ሐሊብ ነው፤ ጭማሪ የሌለበት አንድ ሐሊብ እርሱ ነው። እንዲህ እናምናለን እንዲህም እንታመናለን፤ የሃይማኖትንም ጸሎት እንበል።

The Father is the vine, the Son is the vine and the Holy Spirit is the vine: but it is one vine of life from which all the world tasted. The Father is milk, the Son is milk and the Holy Spirit is milk: but it is one milk1 unmixed. Thus we believe and thus we confess and say the creed.

ወደቀደመው ነገር እንመለስ፤ ቅድስት ድንግልም ለሁሉ ድን
ቅ የሚሆን የዕንሷን ነገር እንዲህ እያልን እንመርምራት።
ድንግል ሆይ! እሳተ መለኮት በሆድሽ ባደረ ጊዜ ፊቱ
እሳት፤ ልብሱ እሳት፤ ቀሚሱ እሳት ነው፤ አንደምን
አላቃጠለሽ። ሰባት የእሳት ነበልባል መጋረጃ በሆድሽ
ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ ወዴትስ ተጋረደ፤ ከጐንሽ በቀኝ ነውን
ወይስ ከጐንሽ በግራ ነውን፤ ትንሽ አካል ስትሆኝ።

Let us now return again to peak of the holy Virgin, speaking of her conception which is wonderful to all, and saying: O Virgin, when there abode in your womb the fire of the Godhead, Whose face is fire, Whose clothes are fire, Whose covering is fire, how did it not burn you?

የሚያንጸባርቅ ነደ እሳት የሚከበው፤ ኪሩቤል
የተሸከሙት ዙፋን በሆድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ፤
ወዴትስ ተተከለ፤ ታናሽ ሙሽራ ስትሆኝ። ከገረድነት ጋራ
እናትነት እንደምን ያለ ነው ከስፋት ጋራ የሆድ መጥበብ
እንደ ንብ ያለ ሩካቤ ከቃል ድምፅ የተገኘ ፅንስ፤

In what part of your womb was the glittering cherubic throne, compassed by the flame of fire, prepared and planted while you were a young bride? How wonderful it is! A mother and a maid ; the narrowness of the womb and the infinite; conception without intercourse,

ከድንግልና ጋራ አንድ የሆነ ሐሊብ። ይህንም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ የልጅሽን የባሕሩን ጥልቅነት ሊዋኝ ይወዳል የወዳጅሽ የመሠወሪያው ማዕበልም የማታዋል።

as a bee conceives, from the voice of a word; milk with virginity. When I think of this, my mind likes to swim in the depth of your Son's seas, and the billows from the hiding-place of your Beloved sweep across it.

ዳግመኛ ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ ተሠውሮ ወደ ላይ ወጥቶ የሕያው መሠወሪይ የሆነውን ሊገልጥ ይወዳል። ከነደ እሳትነቱ የተነሣ ይፈራል ከወየራት ከእርቧቸው እርቦ አይደርስም። ይህንንም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ በነፋስ ትከሻ ተጭኖ በምሥራቅና በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ በዳርቻውም ሁሉ ሊበር ይወዳል።

Again when I think of this my mind likes to soar and ascend secretly and draw back the curtains of the hiding-places of the Living One ; it becomes afraid of the flame of fire and does not reach even one-fourth of the way to heaven. When I think of this my mind likes to mount the shoulders of the winds to fly east, west, north and south to all the ends (of the world)

www.ethiopianorthodox.org

የፍጡራንን አኗኗር ያይ ዘንድ የአብሕርትንም ጥልቅነታቸውን ይለካ ዘንድ የሰማይን ርዝመቱን ያውቅ ዘንድ። በሁሉ ዘንድ በሁሉም ይዞራል። አቅቶት ወደ ቀደመ አኗኗሉ ይመለሳል። አሁንም ገናንነቱን አንመርምር፤ ጥልቅነቱንም አንጠናቀቅ፤ የገናንነቱን መጠን ለማመስገን የነቢያትና የሐዋርያት አንደበት የማይቻለው ነው።

to see the nature of the creatures, to measure the depths of the seas and to know the height of heaven, and travelling thus to every part it becomes faint and returns again to its former place. Now let us not further enquire or even think of the greatness and profundity of Him Whose grandeur cannot worthily be praised, no, not by the tongues of the prophets nor of the apostles.

የማይደፈር ግሩም ነው፤ በእኛ ዘንድ ግን ትሑት ነው። የማይገኝ ልዑል ነው በእኛ ዘንድ ግን አርኣያ ገብርን ነሣ። የማይዳሰስ እሳት ነው አኛ ግን አየነው ዳሰስነውም፤ ከርሱም ጋራ በላን ጠጣን አሁንም እንዲህ እያልን እናመሰግነው።

He is the mighty One Whom none can discern by subtle device but He became humble among us; He is the most high, to Whom none can attain_ but among us He took upon Him the form of a servant; He is the impalpable fire, but we saw Him and felt Him and ate and drank with Him.
Now let us praise Him saying.

(በለሆሳስ ድምፅ)

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው
ዘኢ.ይመውት ዘተንሥአ እሙታን
አመ ሣልስት

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው
የማይሞት በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ
የተነሣ

Holy God, holy Mighty, holy Living, Immortal,
who didst rise from the dead on the third day,

ካህን/Priest

ድንግል ሆይ! የሚበላውን ያፈራሽልን የሚጠጣውን ያስገኘሽልን። ወዮ ከአንቺ የተገኘ ኅብስት በማመን ከርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትንና ደኅንነትን የሚሰጥ ነው። ወዮ ከአንቺ የተገኘ ኅብስት በማመን ከርሱ ለሚቀበሉ ሰዎች የማይለመጥ ጽኑ ነው፤

O Virgin who gives the fruit that can be eaten, and the spring of that which can be drunk O Bread got from you, that gives life and salvation to those who eat of it in faith.

ይኸውም ኃያል የሚሆን የአድማስ ደንጊያ ነው።
ወዮ ከአንቺ የተገኘ ጽዋ በማመን ከርሱ ለሚጠጡ
ሰዎች ጥበብን የሚገልጽ ሕይወትንም የሚሰጥ ነው።

O Bread got from you, that is as hard as the stone of Admas which cannot be chewed, to those who do not eat of it in faith. O Cup got from you, that helps those who drink of it in faith to indite wisdom, and that gives them life.

ወዮ ከአንቺ የተገኘ ጽዋ በማመን ከርሱ ለሚጠጡ ሰዎች የሚያሰክርና የሚያፍገመግም፤ የሚጥልና ኃጢአትን ስለሚያስተው ፈንታ ኃጢአትን የሚጨምር ነው። አሁን ም ለአንተ ምስጋና ይገባሃል። ለመንግሥትህም ምስጋና ይገባል እያልን እናመሰግነው። ከንጹሕ ዕጣን ጋራ ምስጋናን እናቀርብልሃለን።

O Cup got from you, that intoxicates those who do not drink of it in faith and causes them to stumble and fall and adds sin to them instead of the remission of sin And now let us glorify Him saying Glory be to Thee, glory to Thy kingdom, glory with pure incense we offer to Thee.

ሕዝብ/*People*

ተዘከረን እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ። ተዘከረን እግዚኦ
ኦ ሊቅ በውስተ መንግሥትከ። ተዘከረን እግዚኦ በውስተ
መንግሥትከ። በከመ ተዘከርኮ ለፈያታዊ ዘየማን እንዘ
ሀሎከ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ።

አቤቱ በመንግሥትህ አስበን ፤ ሊቅ ሆይ አቤቱ በመን
ግሥትህ አስበን ፤ ሊቅ ሆይ አቤቱ በመንግሥትህ አስበን
፤ ቅዱስ በሚሆን በዕፀ መስቀል ላይ ሳለህ ፈያታዊ
ዘየማንን እንዳሰብከው አቤቱ በመንግሥትህ አስበን።

**Remember us, Lord, in Thy kingdom;
remember us, Lord, Master, in Thy kingdom;
remember us, Lord, in Thy kingdom, as Thou
didst remember the thief on the right hand
when Thou was on the tree of the Holy Cross.**

ካህን/Priest

በጎ ሀብት ሁሉ፤ ፍጹም ዕድል ሁሉ ከርሱ የሚገኝ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆነ፤ ከኃጢአት ብቻ በቀር የሰውን ሕግ ሁሉ ፈጸመ፤ የዕብራውያንንም ሕግ ተማረ።

Jesus Christ, Son of the living God, from Whom is found every good gift and every perfect gift, became man, fulfilled all the law of man yet without sin, and practiced the law of the Hebrews.

ከዮሐንስ ዘንድ ተጠመቀ፤ በገዳም ተፈተነ፤ ተራበ
ተጠማም፤ ተአምራትንም አደረገ።
ሰውነቱን ከሞት በሰጠበት በዚያች ሌሊት ከደቀ
መዛሙርቱ በብዙ ምልክት አመለከተ።

He was baptized by John, tempted in the wilderness, hungered and thirsted and did miracles. . In the same night in which He gave His soul to death He showed His disciples many signs.

የሕማሙንና የስቅለቱን የሞቱን ነገር በሦስተኛም ቀን የመነሣቱን ነገር በነፍስ በአጥንትና በደም ቀደሞ እንደ ነበረው ደቀ መዛሙርቱ ከርሱ ጋራ በቀኙና በግራው ሳሉ ፍጥረቱ ከርዳድ የሚሆን ከስንዴ ጋራ የተቀላቀለ ያስያዘው ይሁዳም ከነርሱ ጋራ የተቈጠረ ሆኖ ነበረ።

concerning His sufferings, crucifixion, death, His re-surrection on the third day with body and soul, with bone and blood, as it was before, when His disciples were with Him on His right and left, and when there was counted with them Judas whose creation was like the tares added to wheat, and who betrayed Him.

ዲያቆን/Deacon

አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት

ቀሳውስት እጆቻችሁን አንሱ

Priests, raise up your hands.

ካህን/Priest

ያን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳት ብዑዓት በሚሆኑ እድፍ በሌለባቸው እጆቹ ኅብስቱን አነሣ።

At that time Jesus Christ took bread in his holy, blessed, pure and spotless hands

ሕዝብ/*People*

ኑአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ኑአምን

ይህ እንደሆነ በእውነት እናምናለን

We believe that this is He, truly we believe.

ካህን/Priest

